# የአካባቢና ማኅበራዊ ተጽዕኖ ግምገማ የጥናት ሪፖርት
# (የተከለሰ)
# የፕሮጀክት ባለቤት፡- ሮሃ ሜዲካል ካምፓስ፣
# ቦሌ ክ/ከተማ፣ ወረዳ 13
# አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

ለኢትዮጵያ አካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን የቀረበ

**አድራሻ፡-** አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

ኦገስት፣ 2024 (እ.ኤ.አ.)

# አዕጽሮተ ጥናት

## መግቢያ

ሮሃ ሜዲካል ካምፓስ ኃ/የተየግ/ማ በኢትዮጵያ ውስጥ ከፍተኛ ጥራትና ተመጣጣኝ ዋጋ ያለው የጤና ክብካቤ አገልግሎት ክፍተት እንዳለ በመረዳት ይህንን ክፍተት ለመሙላት የሮሃ ሜዲካል ካምፓስን በአዲስ አበባ ለመገንባት አቅዷል። ሮሃ ሜዲካል ካምፓስ (ሮሃ) በመሐል አዲስ አበባ የሚገነባ መልቲ-ዲሲፕሊነሪ የጤና ክብካቤ ማዕከል ነው። ሮሃ ሲጠናቀቅ በርካታ ሆስፒታሎችን፣ የተመላላሽ ታካሚ ፋሲሊቲዎችን፣ የምርምርና የፈጠራ ማዕከልን፣ የሕክምና ትምህርት ቤትን፣ ለሳይንስና ለጤና ክብካቤ ኩባንያዎች የሚሆን የቢሮ ፓርክና ሌሎች ተጓዳኝ አገልግሎቶችን የሚያካትት ይሆናል። በአፍሪካ ውስጥ ከሚገኙ ግዙፍ የጤና ክብካቤ የልማት ፕሮጀክቶች መካከል አንደኛው ሲሆን በተለያዩ ምዕራፎች በሚቀጥሉት 5-10 ዓመታት ይጠናቀቃል ተብሎ ይጠበቃል። ሮሃ በመሐል አዲስ አበባ የሚገኝ ትልቅ ቦታ አግኝቷል።

ይህ ሰነድ የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን (በፊት "የአካባቢ፣ የደን እና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን (አ.ደ.አ.ን.ኮ) ያጸደቀው የአካባቢና ማኅበራዊ ተጽዕኖ ግምገማ (እ.ኤ.አ 23 ዲሴምበር 2021፣ ቁጥር 9/1.1/6131.14) ላይ ማሻሻያዎች ተደርገውበት የቀረበ ነው። ማሻሻያው፣ ሃያ ሁለት (22) ሄክታር የሚሆን የሮሃ ቦታ ለሌሎች የመንግስት ፕሮጀክቶች የሚተላለፍ መሆኑን ከግምት የሚያስገባ በመሆኑ ለፕሮጀክቱ ዘላቂነት ቁልፍ ሚና እንደሚኖረው ይታሰባል። በመሆኑም፣ ይህ ማሻሻያ አሁን በሮሃ ይዞታ ሥራ ባለው ስድስት (6) ሄክታር ቦታ ውስጥ የሚኖሩትን ተመጣጣኝ ኃላፊነቶች የያዘ ነው። በተጨማሪም ይህ የፕሮጀክቱ ክንውን እየተካሄደ በመሆኑ እንደ የወለል ፕላኖች፣ የውኃጅ አስተዳደርና የመሳሰሉ አገልግሎቶች ዝርዝር ዕቅዶችና በጀቶች በዚህ በተሻሻለው ሪፖርት ውስጥ ተካትተዋል።

# የፕሮጀክቱ አጠቃላይ ቅኝት

## ግቦችና ዝርዝር ዓላማዎች

ሮሃ ፣ 1,100 አልጋዎች ያሏቸውን ከፍተኛ ስፔሻልቲዎችን እንዲሁም ዘመን አፈራሽ ቴክኖሎጂዎችን ያካተቱ አምስት ሆስፒታሎችን፣ የሕክምና ትምህርት ቤትንና ሌሎች የአገልግሎት ሕንጻዎችን የሚይዝ ነው። ሁሉንም የታሰቡትን ልማቶች ለማጠናቀቅ በግምት 300 ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር የሚፈጅ ይሆናል።

የሮሃ የመጀመሪያው ክፍል ("ክፍል 1" ወይም "ፕሮጀክቱ") የረቀቀ የባለ ብዝኀ-ስፔሻልቲ ሆስፒታልን መክፈትንና አጠቃላይ የካምፑሱን ማስተር ፕላን ማጠናቀቅን የሚያካትት ነው። የመጀመሪያው ሆስፒታል እስከ 350 አልጋዎችን የሚይዝና ጠቅላላ ስፋቱ 38,000 ካሬ ሜትር ሲሆን አጠቃላይ የስፔሻልቲ አማራጮችን የሚይዝ ነው። ማስተር ፕላኑን የማዘጋጀቱ ሒደት ዓለም አቀፍ ባለሞያዎች የሚሳተፉበትና ባለ ብዝኀ-ዓመት ልማትን መሠረት በማድረግ ለመላው የስድስት (6) ሄክታር መሬት የሚሆን የትግበራ ዕቅድ ይመነጭበታል ተብሎ ይጠበቃል።

በአሁኑ ወቅት የታቀደው ብዙ ስፔሻልቲዎችን የሚይዘው ሆስፒታል በግንባታ ላይ ሲሆን ጎን ለጎን የኦፕሬሽን ዕቅድ ዝግጅት እየተከናወነ ነው። ሆስፒታሉ እ.ኤ.አ. በ2026 አገልግሎት መስጠት ይጀምራል። ከዚህ ሌላ ፕሮጀክቱ ከዚህ በፊት በይዞታው ሥር ለሚገኘው 28 ሄክታር መሬት የመልሶ ማስፈር ዕቅድ ተግብሯል፤ 12,000 የሚሆኑ 35 ልዩ ልዩ ዝርያዎች ያሏቸው አገር-በቀል ዛፎችን ተከሏል። የዚህ የአካባቢና ማኅበራዊ ተጽዕኖ ግምገማ ጥናት ዓላማ የጤና ክብካቤ ፋሲሊቲውን ዋና ዋና አዎንታዊና አሉታዊ ተጽዕኖዎች መለየት እንዲሁም ከአማራጭ ትንተናዎች ጋር የሚያያዙ የተጽዕኖ ማቅለያ እርምጃዎችን መቀየስ ነው። ሪፖርቱን ለማጠናቀር ከቀደምት እና ድህረ የመረጃ ምንጮች ተሰብስቧል። ተጽዕኖ ከደረሰበት ማኅበረሰብና በቦሌ ክፍለ ከተማ፣ ወረዳ 13 እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውስጥ ከሚገኙ ባለድርሻ ቢሮዎች ጋር ምክክሮች ተካሂደዋል።

## የፕሮጀክት አማራጭ

ባዮፊዚካል፣ ማኅበረ-ኢኮኖሚያዊና ቴክኒካዊ ሁኔታዎችን ከግምት በማስገባት የተለያዩ የፕሮጀክት አማራጮች ተፈትሸዋል። የተፈተሹት አማራጮች:-

- የአማራጭ ፕሮጀክት አለመኖር
- የፕሮጀክት መስክ አማራጮች
- የፕሮጀክት የጊዜ ሰሌዳ አማራጮች
- የፕሮጀክት ንድፍ አማራጮች ናቸው።

ቴክኒካዊ ተፈጻሚነትን፣ ኢኮኖሚያዊ አዋጪነትንና የአካባቢያዊ ተጽዕኖን ታሳቢ በማድረግ ሲተነተን በሃሳብነት የቀረበው ፕሮጀክት በዚህ ጊዜ ከሁሉም የተሻለው አማራጭ ሆኖ ተገኝቷል። ለከተማው ጤና እና ኢኮኖሚ የሚኖረውን ጠቀሜታ እንዲሁም በማኅበራዊና ባዮፊዚካል ከባቢው ላይ የሚኖረውን ዝቅተኛ ተጽዕኖ ስንመለከት ፕሮጀክቱ አጠቃላይ አዎንታዊ አስተዋጽዖ እንዳለው መደምደም ይቻላል።

## የፕሮጀክቱ መገኛ

ፕሮጀክቱ በአዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ፣ ቦሌ ክ/ከተማ፣ ወረዳ 13 ከዚህ በታች በተመለከቱት የጂፒኤስ ኮኦርዲኔቶች ላይ የሚገኝ ነው:-

38.7990624554134, 8.99596804879402: 38.7968940841604, 8.99665577491354:
38.7965150900542, 8.99591102525657: 38.7961102107737, 8.99476572934434:
38.7961142284343, 8.99475750148445: 38.7980780582021, 8.99419399722231:
38.7988368967273, 8.99452565776149: 38.7990624554134, 8.99596804879402

ፕሮጀክቱ ከቦሌ ዓለም አቀፍ አየር ማረፊያ በቅርብ ርቀት የሚገኝ ሲሆን ከአየር ማረፊያው ወደ ዳያስፖራ አደባባይ በሚወስደው የቀለበት መንገድ በኩል ይገኛል (ከታች ያለውን ምስል ይመልከቱ)።




## ተቋማዊና ሕጋዊ ማዕቀፎች

እ.ኤ.አ. በ2000 በወጣው የኢትዮጵያ የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ መመሪያ መሠረት ሊለማ የታሰበው ሆስፒታል በሰንጠረዥ 1 ሥር የሚገኝ በመሆኑ በአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ከመጽደቁ በፊት አጠቃላይ የአካባቢና ማኅበራዊ ተጽዕኖ ግምገማ (አ.ማ.ተ.ግ) ማከናወን አለበት። በመሆኑም ሮሃ ሜዲካል ካምፓስ (“አልሚ”) የአ.ማ.ተ.ግ ጥናቱን እንዲያካሂድ “[redacted]” የተባለውን አማካሪ ድርጅት ቀጥሯል።

የጥናቱ ወሰን በፕሮጀክቱ ዐበይት የአካባቢያዊና ማኅበራዊ አካላት ላይ ያተኮረ ሲሆን እነዚህም የመስክና የሰነድ ዳሰሳን መሠረት በማድረግ የተለዩ ናቸው። የመስክ ቅኝቶች፣ በፕሮጀክቱ ተጽዕኖ ሊደርስባቸው የሚችሉ የተለያዩ ተፈጥሮአዊና ሰው-ሰራሽ አካባቢያዊ አሃዶች መኖራቸውን ያመላክታሉ። እነዚህም የመንግስት ትምህርት ቤቶችን፣ ነዋሪዎችን፣ አነስተኛና ጥቃቅን ኤንተርፕራይዞችንና ቤቶችን እንዲሁም የኮንክሪት ማምረቻዎችን ያካትታሉ።

የአ.ማ.ተ.ግ ጥናቱን አፈጻጸም ተቋማዊ አሠራሮችን በሚመለት የስትራቴጂዎችን፣ ፖሊሲዎችን፣ ሕጎችንና ስታንዳርዶችን እንዲሁም የአሠራሮችን ቀረጻ የማስጀመርና የማስተባበር ጥናቶች ሲጸድቁም አተገባበራቸውን የመከታተልና የማስከበር ኃላፊነት የተሰጠው የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ነው። ከዚህም በተጨማሪ የዓለም አቀፍና ቀጠናዊ ስምምነቶች ትግበራና ክትትል ኃላፊነት አለበት። ይኸው መሥሪያ ቤት የአ.ማ.ተ.ግ ሪፖርቶችን የመገምገምና የማጽደቅ እንዲሁም ፈቃድ የመስጠት ሥልጣን ያለው ከመሆኑ በተጨማሪ ለአ.ማ.ተ.ግ ባለሞያዎች ፈቃድ የሚሰጥም ነው። ባለሥልጣኑ በክልል ደረጃዎች ቢሮዎች እንዲሁም በየወረዳዎች መኮንኖች ያሉት ቢሆንም ይህ ፕሮጀክት በኢትዮጵያ ኢንቬስትመንት ኮሚሽን ሥር የተመዘገበ በመሆኑ አልሚው የአ.ማ.ተ.ግ ጥናቱን እንዲያጸድቅለት የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣንን መጠየቅ ይችላል።

የኢትዮጵያ መንግስት እንዲሁም እንደ ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ድርጅትና የአፍሪካ ልማት ባንክ ያሉ ተቋማት ያወጧቸው ልዩ ልዩ ፖሊሲዎች፣ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በአ.ማ.ተ.ግ ጥናቱ ውስጥ እንዲካተቱ ተደርገዋል።

ከተመለከትናቸው አገራዊ የሕግ ሰነዶች መካከል:-
የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ-መንግስት፣ የኢትዮጵያ የአካባቢ ጥበቃ ፖሊሲ (እ.ኤ.አ. 1997)፣ የውሃ ሀብት አስተዳደር ፖሊሲ፣ የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ አዋጅ (299/2003)፣ የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር አዋጅ (200/2002)፣ የማኅበረሰብ ጤና ፖሊሲ አዋጅ (200/2000) ይገኙበታል። ዓለም አቀፍ የልማት ፋይናንስ ተቋማትን በሚመለከት ደግሞ የሚከተሉት መመሪያዎችን ተመልክተን አካትተናቸዋል።

የአፍሪካ ልማት ባንክ የኦፕሬሽን ከለላዎች:-

- E&S OS 1 (OS1): የአካባቢና ማኅበራዊ ስጋቶች እና ተጽዕኖዎች ግምገማና አስተዳደር
- E&S OS 2 (OS2): ሠራተኞችና የሥራ ሁኔታዎች
- E&S OS 3 (OS3): የሀብቶች የተቀላጠፈ አጠቃቀም እንዲሁም ብክለትን መከላከልና ማስተዳደር
- E&S OS 5 (OS5): የመሬት ግኝት፣ መሬትን የማግኘት የመጠቀም መብት ገደቦች እና ያለፈቃድ ሰዎችን መልሶ ወደ ሌላ ቦታ ወስዶ ማስፈር
- E&S OS 10 (OS10): የባለድርሻዎች ተሳትፎና የመረጃ አገላለጽ

የአይ.ኤፍ.ሲ. የአፈጻጸም ስታንዳርዶች:-

- የአካባቢያዊና ማኅበራዊ ተጽዕኖ ግምገማ (PS 1)
- ሠራተኞችና የሥራ ሁኔታ (PS 2)
- የሀብት አጠቃቀም ቅልጥፍናና ብክለትን መከላከል (PS 2)
- መሬትን ማግኘትና ያለ ፈቃድ ነዋሪዎችን በሌላ ቦታ ማስፈር (PS 5)
- ብዝኀ-ሕይወት ጥበቃና ሕያው ዘላቂነት ያለው የተፈጥሮ ሀብቶች አስተዳደር (PS 6)
- የባለ ድርሻዎች ተሳትፎና የመረጃ አገላለጽ (PS 10)

## የፕሮጀክት ተጽዕኖዎች

ግምገማው ታሳቢ ያደረገው ፕሮጀክት በሺዎች ለሚቆጠሩ ዜጎች (5000-7000) የሥራ ዕድል መፍጠርን ጨምሮ በርካታ የማኅበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታዎች እንደሚኖሩት አመላክቷል። በሜዲካል ቱሪዝም ረገድም የውጭ ምንዛሬን ለማመንጨትና ለማዳን ያስችላል። የዜጎችን ጤናና ምርታማነት ከማረጋገጡም በላይ ታካሚዎች ጥራት ያለውን የጤና ክብካቤ ፍለጋ ወደ ውጪ ከመጓዝ አገልግሎቱን እዚሁ እንዲያገኙ ዕድል ይሰጣል። በተጨማሪም  እንደ ትራንስፖርትና ምግብ ባሉ አገልግሎቶች እንዲሁም በፍጆታ ምርቶች ግብይት የአካባቢው የንግድ እንቅስቃሴ ላይም አዎንታዊ ሚና ይጫወታል።

በሌላ በኩል ፕሮጀክቱ በርካታ አሉታዊ ተጽዕኖዎችም ሊኖሩት ይችላሉ። ከእነዚህም መካከል በቅድመ-ግንባታው ወቅት የሚጠበቀው ዋነኛ አሉታዊ ተጽዕኖ በፕሮጀክቱ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎችን ወደሌላ ቦታ ከማስፈር ጋር የሚገናኝ ነው። በኦፕሬሽን ወቅት የሚኖሩ ዐበይት ተጽዕኖዎች ከጠጣር እና ፈሳሽ ውጋጆች እንዲሁም ትክክለኛ ባልሆነ መቀጣጠል ከሚፈጠር የአየር ብክለት ጋር የተገናኙ ናቸው። ይህ ፕሮጀክት ቢተገበር ብለን የምንመክራቸው ዋና ዋና የተጽዕኖ ማቃለያ እርምጃዎች ተጽዕኖ ከሚደርስበት ማኅበረሰብ ጋር ተገቢ ምክክሮች፣ ተገቢ የውጋጅ ቅነሳና ልየታ፣ ተገቢ የማቃጠል አሠራሮች እንዲሁም ተገቢ የሆነ የመስክ መረጣ (የነፋስ አቅጣጫን፣ ስነ-ውበታዊ ተጽዕኖንና ተጽዕኖ የሚደርስበትን አካባቢ መሠረት በማድረግ) እንዲሁም ተገቢ የማቃጠያዎች ዲዛይን ናቸው።

የጥናቱ ወሰን የፕሮጀክቱን ዐበይት የአካባቢያዊና ማኅበራዊ አካላት ላይ ያተኮረ ሲሆን እነዚህም የመስክና የጽሑፎች ቅኝትን መሠረት በማድረግ የተለዩ ናቸው። የመስክ ቅኝቶች፣ በፕሮጀክቱ ተጽዕኖ ሊደርስባቸው የሚችሉ የተለያዩ ተፈጥሮአዊና ሰው-ሰራሽ አካባቢያዊ አሃዶች መኖራቸውን ያመላክታሉ። እነዚህም የመንግስት ትምህርት ቤቶችን፣ ነዋሪዎችን፣ አነስተኛና ጥቃቅን ኤንተርፕራይዞችንና ቤቶችን እንዲሁም የኮንክሪት ማምረቻዎችን ያካትታሉ። የዚህ የአካባቢና ማኅበራዊ ተጽዕኖ ግምገማ ጥናት ዓላማ የጤና ክብካቤ ፋሲሊቲውን ዋና ዋና አዎንታዊና አሉታዊ ተጽዕኖዎች መለየት እንዲሁም ከአማራጭ ትንተናዎች ጋር የሚያያዙ የተጽዕኖ ማቅለያ እርምጃዎችን መቀየስ ነው። ሪፖርቱን ለማጠናቀር ከቀዳሚና እና ሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ተሰብስቧል። ተጽዕኖ ከደረሰበት ማኅበረሰብና በቦሌ ክፍለ ከተማ፣ ወረዳ 13 እና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውስጥ ከሚገኙ ባለድርሻ ቢሮዎች ጋር ምክክሮች ተካሂደዋል።

## ከማኅበረሰቡ ጋር የተደረገ ምክክር

ከ100 በላይ ተሳታፊዎች የተገኙበት ምክክር ግንቦት 07 ቀን 2013 ዓ.ም ተካሂዶ ነበር። በዚህ ምክክር ወቅት ሁሉም ተሳታፊዎች ሊባል በሚችል ደረጃ ሜዲካል ካምፑሱ ለአካባቢው ማኅረሰብ በአጠቃላይ እንደ አገር የሚኖረውን ጠቀሜታ አንስተው ፕሮጀክቱን ተቀብለውታል። ሆኖም መንግስት የሥነ-ልቦናና ኢኮኖሚያዊ ዝግጅት እንዲያደርጉ በቂ ጊዜ እንዳልሰጣቸውና ይህም በግድ እንዲፈናቀሉ እንዳደረጋቸው እንጂ ዘላቂነት ያለውና ጊዜውን ያማከለ መፍትሔ እንዳልሰጣቸው ቅሬታቸውን ገልጸዋል። በዚህም ምክንያት በቦታው የነበሩ የጨረቃ ሰፋሪዎችንና ተከራይተው ነዋሪዎችን ጨምሮ በርካታ ነዋሪዎች መተዳደሪያ እንዳይኖራቸው ሆነዋል። አብዛኛዎቹ ተሳታፊዎች ሮሃ በቀጥታ ተጽዕኖ የደረሰባቸውን ሰዎች የትምህርት ደረጃና የሥራ ልምድን በመመልከት በማስቀደም በፕሮጀክቱ የተለያዩ ደረጃዎች ውስጥ የሥራ ዕድል እንዲያገኙ እንዲያደርግ ሀሳብ ሰጥተዋል። ከዚህም በተጨማሪ የተጀመረው የመልሶ ማስፈር ዕቅድ ግልጽ፣ ትክክለኛና ተጽዕኖ የሚደርስባቸው አባወራዎች ለአላስፈላጊ ድኅነት የመጋለጣቸውን አደጋ ማቃለል እንዲቻል አስቀድሞ ስለ መልሶ ማስፈር ፕሮጀክቶች ዝርዝር መረጃን የሚያካትት መሆን እንዳለበት ተናግረዋል።

## የአካባቢና ማኅበራዊ አስተዳደር ምንጮች

አካባቢያዊና ማኅበራዊ ተጽዕኖዎችን ለመቀነስ የሚሆኑት ዋና ዋና የማቃለያና የመከታተያ እርምጃዎች በፕሮጀክት የማቃለያና የማስተዳደሪያ ዕቅዶች መሠረት የሚተገበሩ ይሆናል። በተመሳሳይም የማቃለያ እርምጃዎች ትግበራ በአካባቢያዊና ማኅበራዊ ክትትል ዕቅዱ መሠረት ከተቀመጠው በጀት አንጻር የሚረጋገጥ ይሆናል።

ይህ ክትትል በኩባንያው ሥራ መሪዎች በመደበኛነት መከናወን ያለበት ነው። የኩባንያው ሥራ አመራር ቡድን ከከተማው የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን/ወይም የክ/ከተማ እና ወረዳ ቢሮዎች እንዲሁም ከአካባቢው ማኅበረሰብ ተወካዮች ጋር በመሆን የአካባቢያና ማኅበራዊ አስተዳደር ዕቅዱን አፈጻጸም በተወሰነ ጊዜ አንዴ መከታተል አለባቸው።

## የአካባቢና ማኅበራዊ አስተዳደር ዕቅድ (አ.ማ.አ.ዕ)

ይህ አ.ማ.ተ.ግ ፕሮጀክቱ ሊያስከትላቸው የሚችሉ ተጽዕኖዎችን በመዳሰስ የስጋት ቅነሳ ተግባራት ለማቀድ ያለመ ነው። የሚከተለው ሰንጠረዥ ተጽዕኖዎችና የማቅለያ ተግባራቱ የሚመለከቱትን አካልና ተያያዥ ወጪዎችን በግልጽ የሚያስቀምጥ ነው:-

| የተጽዕኖ መግለጫ | የማቃለያ መፍትሔዎች | አመላካቾች | ኃላፊነት ያለበት አካል | ጊዜ | አዲስ መረጃ | ወጪ (ብር)/ዓመት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| **የልማት ተነሺዎች** | - የመልሶ ማስፈር ሒደቱን አስመልክቶ ከነዋሪዎች ጋር መመካከር ያስፈልጋል።<br>- አልሚው የኢትዮጵን ሕግና ዓለም አቀፍ መርሆችን ባከበረ መልኩ በፕሮጀክቱ ተጽዕኖ ለደረሰባቸው 136 አባወራዎች መልሶ የማስፈር ዕቅድ (መ.ማ.ዕ) እና የመተዳደሪያ ምልሰት ዕቅድ (መ.ም.ዕ) አዘጋጅቷል።<br>- ፕሮጅቱ ለ136 አባወራዎች የመተዳደሪ ምልሰት ዕቅድን የሚያካትት የመልሶ ማስፈረር ዕቅድ እየተገበረ ነው። ፕሮጀክቱ ለጨረቃ ሰፋሪዎች የመተዳደሪያ ድጋፍ ክፍያ ያደርጋል፣ የክህሎት ሥልጠናዎችን በመስጠት በሜዲካል ካምፐሱ ግንባታና አፕሬሽን ወቅት የአካባቢውን ሰዎች ይቀጥራል።<br>- ለልማት ተነሺዎች በተለይም ለ8 አባወራዎች በአፋጣኝ አማራጭ የመስፈሪያ ቦታ ሊቀርብ ይገባል።<br>- የልማት ተነሺዎች ቀጣይነት/ዘላቂነት ያላቸውን መተዳዳሪያዎች ስለሚሠሩበት መንገድ ምክር ሊያገኙ ይገባል። | ከማኅበረሰቡ ጋር የሚደረግ ምክክር፣<br><br>የመ.ማ.ዕ ዝግጅት | የፕሮጀክቱ ባለቤት (ሮሃ ሜዲካል ካምፓስ “ሮ.ሜ.ካ”)<br><br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ አካባቢ ጥበቃ ቢሮ<br><br>በቦሌ ክ/ከ የመሬት አስተዳደር ቢሮ | ከፕሮጀክቱ ግንባታ በፊት | የመጀመሪያወው ምክክር ጃንዋሪ 2021 ላይ ተካሄደ<br><br>መ.ማ.ዕ እና መ.ም.ዕ ኤፕሪል 2021 ላይ ተዘጋጁ።<br><br>ለ38 አባወራዎች ሙሉ ካሳ ክፍያ እንዲሁም ለ98 አባወራዎች የመተዳደሪያ ማሻሻያ ክፍያዎች ተፈጽመዋል።<br><br>በመ.ማ.ዕ መሠረት ለ38 አባወራዎች መልሶ የሚሰፍሩበት አማራጭ ቦታ ቀርቧል። | 28,000,000 (የአንድ ጊዜ) |
| **የአየር ብክለት** | - አላስፈላጊ የተሸከርካሪ እንቅስቃሴዎችን ማስቀረትና ተገቢ የጊዜ ሰሌዳ ማስቀመጥ<br>- በወጣ መንገዶች ላይ የተሸከርካሪዎችን ፍጥነት መገደብ፤<br>- መሣሪያዎችንና ተሸከርካሪዎችን በአግባቡ ጠግኖ በመያዝ ከመጠን ያለፈ ልቀትን ማስቀረት፣<br>- በኦፕሬሽን ወቅት የአቧራ ብክለትን ለመቀነስ የተቆፈሩ ቦታዎች ላይ በየጊዜው ውሃ ማርከፍከ<br>- የግንባታ ሥራው መከናወን ያለበት በአግባቡ በተመዘገበ፣ ስለ አካባቢ ጥበቃ ግንዛቤ ባለውና ኀላፊነት በሚሰማው ተቋራጭ መሆን አለበት።<br>- የግል ደኅንነት መጠበቂያዎች (ግደመ) ለሠራተኞች እንዲቀርቡ ማድረግና ሠራተኞችም እንዲጠቀሟቸው ማስገደድ ያስፈልጋል።<br>- አቧራን ለመቀነስ ግብአቶች ከገልባጮች ላይ ሲገለበጡ ከተገቢው ከፍታ መሆን አለበት።<br>- ከባድ መኪኖች ዋና የካርቦን ሞኖክሳይድና የናይትሪክ አክሳይድ ምንጭ በመሆናቸው ብክለቱን ለመቀነስ በተገቢው መንገድ በመደበኛነት መጠገን አለባቸው።<br>- የአቧራ ብናኝ ትንፈሳን ለመቀነስ ለሠራተኞች የፊት ማስክ መቅረብ አለበት። | የ “በፈር ዞን” ይለያል ይከበራል<br><br>ከማኅበረሰብ የሚመጣ ቅሬታ<br><br>የአቧራ መፈጠር | ሮሃ<br><br>ተቋራጭ | በግንባታ ወቅት | ልምድ ያለው ደረጃ አንድ ተቋራጭ ተቀጥሯል።<br><br>የአ.ማ.ማ.ዕ ላይ የሚገኙትን የአየር ብክለት ማስተካከያ እርምጃዎች እንዲተገብር ለኮንትራክተሩ አ.ማ.ተ.ግ እንዲሰጠው ተደርጓል።<br><br>የቀረበ ቅሬታ የለም። | 400,000 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | - የግንባታ ዕቃዎችንና ፍርስራሽ የጫኑ ተሽከርካሪዎች በሸራ መሸፈን አለባቸ<br>- ጥሬ ዕቃዎች፣ ተቆፍሮ የወጣ ዐፈርና ሌሎች በናኞች መከማቸትም ሆነ መጓጓዝ ያለባቸው በተሸፈኑ መረቦች ሥር መሆን አለበት፤<br>- አቧራ እንዳይነሳ ለማድረግ ከቁፋሮ በፊትና በኦፐሬሽን ወቅት በመደበኛነት ውሃ መርጨት፤<br>- በግንባታ ላይ ያሉ መዋቅሮችን በአቧራ መከላከያ መረቦች መሸፈን<br>- በማንዋሉ መሠረት ማሽኖችንና ሞተሮችን በመደበኛነት መጠገን፤ | | | | | |
| **የድምጽ ብክለት** | - በማንዋሉ መሠረት መሣሪያዎችን በትክክለኛው ጊዜ መጠገን፤<br>- ከመደበኛ የሥራ ሰዓት ውጪ የሚከናወን የግንባታ ሥራ የፕሮጀክት አስተዳዳሪውን ፈቃድ ማግኘትና አስፈላጊ ሲሆን በአቅራቢያ ላሉ ነዋሪዎች ማስጠንቀቂያ መስጠት ያስፈልጋል<br>- ከ85 ዴሲቤል በላይ የሆኑ ድምጾች የሚፈቀዱት አስቀድመው የጸደቁ ከሆኑና ለአቅራቢው ነዋሪዎች ማስጠንቀቂያ (ቢያንስ ከ2 ቀን በፊት) ከተሰጠ ብቻ ነው፤<br>- ከፍተኛ ረብሻ የሚፈጥር ድምጽ ያለው ሥራ መከናወን ያለበት ቀን ብቻ ሲሆን ከላይ የተቀመጠው ማስጠንቀቂያ መሰጠት አለበት፤<br>- በግንባታ ሳይቶች ላይ የድምጽ ብክለትን ለመቀነስ የናፍጣ ጀነሬተሮች የድምጽ ማፈኛ ሽፋን ሊኖራቸው ይገባል፤<br>- በቁፋሮ ሳይቶች፣ የፈረሳ ሳይቶች ላይ ጊዜያዊ የድምጽ መከላከያዎችን ማድረግ፤<br>- ከፍተኛ ድምጽ ባለባቸው ቦታዎች ላይ በሚሠሩ ወይም ከፍተኛ ድምጽ ባላቸው መሣያዎች አካባቢ ለሚሠሩ የጆሮ መሸፈኛና ሌሎች መጠበቂያ መሣሪያዎችን መስጠት<br>- የግንባታ ሥራዎች በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ብቻ መከናወን አለባቸው፤ | ቅሬታ<br><br>በቦታው በአካል በመገኘት የሚደረግ ቅኝት | ተቋራጭ፣ ሮሃ | በግንባታ ወቅት | አ.ማ.ማ.ዕ ላይ የሚገኙትን የድምጽ ብክለት ማስተካከያ እርምጃዎች እንዲተገበር ለኮንትራክተሩ አ.ማ.ተ.ግ እንዲሰጠው ተደርጓል።<br><br>በፕሮጀክቱ ባለቤትና ተቋራጩ መደበኛ ፍተሻ<br><br>የቀረበ ቅሬታ የለም | 100,000 |
| **የውሃ ሀብት ብክለት** | - በውሃ ማጠራቀሚያ ታንከሮች የሚንጠባጠብ ፍሳሽ እንዳይኖር በየጊዜው መፈተሽ፣<br>- ተቆፍሮ የወጣ አፈር፣ ጥሬ ዕቃና የግንባታ ብናኝ እንዳይቆለል ተገቢውን የአያያዝና የአወጋገድ መመንገድ መከተል፣<br>- በኮንክሪት ርጭት ወቅት በመርጫ በመርጨት አላስፈላጊ ፍሰትን መቀነስ፣<br>- በጎርፍ ውሃ ማፋሰሻ ውስጥ የሚጠራቀመውን አፈር ለማስቀረት የጎረርፍ ውሃ ማፋሰሻን የአሸዋ ከረጢት ካለባቸው የዝቃጭ ማጠራቀሚያዎች ጋር ማዘጋጀት፣<br>- ከሠራተኞች ካምፕ የሚመጣ ፍሳሽ ወደ ውሃ አካላት እንዳይገባ ለመከላከል ሴፕቲክ ታንኮችን መገንባት፣<br>- ውጋጆች ከቀሪ (run-off) ውሃ ጋር ተቀላቅለው ወደ ውሃ አካላት እንዳይገቡ ለመከላከል የግንባታና የነዋሪዎች ውጋጅን በተገቢው መንገድ መሰብሰብ፣ ማስተዳደርና ማስወገድ እንዲሁም<br>- የግንባታ ተሽከርካሪዎችና ማሽኖች የዘይት ፍሳሽ እንዳላቸው በየጊዜው መፈተሽ ይኖርባቸዋል። | የላብራቶሪ ፍተሻ እንዲሁም እንደ አስፈላጊነቱ የመስክ ቅኝት | ተቋራጭ፣ ሮሃ | በግንባታ ወቅት | አ.ማ.ማ.ዕ ላይ የሚገኙትን የ[ውሃ] ብክለት ማስተካከያ እርምጃዎች እንዲተገበር ለኮንትራክተሩ አ.ማ.ተ.ግ እንዲሰጠው ተደርጓል።<br><br>የወንዝ ውሃ ምርመራና መደበኛ ፍተሻዎች በተቋራጩና ባለቤቱ ተደርገዋል። | 385,000.00 |
| **በአፈር ላይ የሚደርስ ተጽዕኖዎች** | - ከምችቶች በኋላ የተክል ዕድገትን በሚገድቡ ማለስለሻ ቅባቶች፣ ናፍጣ፣ ቤንዚን፣ ቆሻሻ ወይም ሌላ መበከል የለባቸውም፤<br>- የማንኛውንም ኬሚካል መደፋትና መፍሰስን ይከላከሉ፤ | የመስክ ቅኝት | ተቋራጭ፣ ሮሃ | በግንባታ ወቅት | የአ.ማ.ማ.ዕ ላይ የሚገኙትን የአፈር ብክለት ማስተካከያ እርምጃዎች እንዲተገበር | 200,000.00 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | - ሽርሽራን ለመካለከል የአፈር ጥበቃ እርምጃዎችን መውሰድ። በቁፋሮ አካባቢዎች ዙሪያ ጉድጓድ በመቆፈር ዕላፊ ውሃ ወደ ዝቅተኛ አካባቢ እንዳይፈስ ይከላከሉ። ሽርሽራን ለመከላከል በዝናብ ወቅት ቁፋሮ አያከናውኑ፤ የናፍጣና የሃይድሮሊክ ዘይት ፍሳሽ ለመከላከከል ለመሣሪያዎች መደበኛ ጥገና ያድርጉ፤<br>- የነዳጅ ማከማቻው አካባቢ በአግባቡ መነጠፍ/መጠረግ አለበት፤<br>- የግንባታ ብናኞች በተሸፈኑ ማከማቻዎችና በተነጠፉ ቦታዎች ሥር መቀመጥ አለባቸው። ለዚሁ በተለዩ ሳይቶች ላይ መወገድ አለባቸው።<br>- ከሠራተኞች ካምፕ የሚመጣ ፍሳሽ መስክ ላይ ሊለይ ይችላል። የምግብ ውጋጅ/ርጥብ ውጋጅ በሳይቱ ላይ በሚገኙ ጉድጓዶች ውስጥ ኮምፖስት መደረግ አለበት።<br>- ሪሳይክል የሚደረግ ውጋጅ ፈቃድ ላላቸው ነጋዴዎች መሸጥ፤ ቀሪው ደግሞ የውጋጅ አስተዳደር ኀላፊነት ባላቸው የአካባቢው የመንግስት አካላት አማካኝነተት እንዲወገድ መደረግ አለበት።<br>- ተገቢ የጠጣር ውጋጅ አያያዝ አሠራር (ልየታ፣ መሰብሰብ፣ ማጓጓዝ፣ መልሰሶ መጠቀም፣ ሪሳይከከል፣ መልሶ ማግኘትና ማስወገድ) መኖር አለበት። | የላይ አፈር ንጣፍ ክምችት (ቁልል) | | | ለኮንትራክተሩ አ.ማ.ተ.ግ እንዲሰጠው ተደርጓል።<br><br>ባለቤቱና ተቋራጩ መደበኛ ፍተሻዎችን አድርገዋል። | |
| **የብዝኀ-ሕይወት ተጽዕኖዎች** | - ፕሮጀክቱ በሳይቱ ውስጥ ከፍተኛ የብዝኀ-ሕይወት ዕሴት ያላቸው እና/ወይም የሥነ--ምኅዳር አገልግሎት የሚሰጡ ልዩ ልዩ አገር በቀል የዛፍ ዝርያዎችን ለመትከል የሚሆን ቦታ በመለየት እንዲሁም የምኅዳር መበታተንን የሚቀንሱ እንደ ባዮሎጂካል ኮሪደር፣ በኦፕሬሽን ወቅት/በኋላ ምኅዳሮችን ወደ ነበሩበት የመመለስ ያሉ ርመምጃዎችን በመውሰድ ይህንን ተጽዕኖ ማቃለል ይችላል።<br>- ብዝኀ-ሕይወትን መጠበቅ፣ የሥነ-ምኅዳር አገልግሎቶችን ማስጠበቅና ሕይወት ያላቸውን የተፈጥሮ ሀብቶች ዘላቂነትን ባማከለ መንገድ ማስተዳደር ለዘላቂ ዕድገት ቁልፍ ናቸው።<br>- የዕጽዋት ምንጣሮ ለመንገድ ጥርጊያ ና የጉድጓድ ቁፋሮ ተግባራት እስኪሚያስፈልገው ዝቅተኛ መጠን ብቻ መገደብ አለባቸው። የላይኛው አፈር ንጣፍና የዛፎች ጥልቅ ሥርን ማወክ በተቻለ መጠን ዝቅተኛ መሆን አለበት።<br>- ከኦፕሬሽን ሥራዎችን ቀጥሎ የሚከናወኑ የመልሶ ማልማት ተግባራት ተገቢ ቁጥር ያላቸው አገር በቀል ዝርያዎች መተከላቸውንና በመልሶ ማልማት ዕቅዱ መሠረት መከናወናቸውን ማረጋገጥ፤<br>- የገጸ-ምድር የአትክልት ሥፍራዎች፣ ርከኖችንና የዕጽዋትና የአትክልት ሥፍራዎችን ጥበቃ ማከናወን፣<br>- ምንጣሮን በግንባታ ቦታዎች ብቻ መወሰንና ምንጣሮ የማይደረግባቸውን ቦታዎች በምልክት መለየት | የማደስ/ምልሰት ስትራቴጂዎች መኖር | ተቋራጭ፣ ሮሃ | በግንባታ ወቅት | ባለቤቱ 12,000 የአካባቢው አገር በቀል ዛፎችን ሳይቱ ላይ ተክሏል።<br><br>ለግንባታ አመቺ እንዲሆን 8 ዛፎች ከነበሩበት ተነቅለው ሌላ ሥፍራ ላይ ተተክለዋል። | 10,260,000 |
| **የመገልገያዎች ተጽዕኖዎች** | - የውሃ ቁጠባ ቴክኒኮችን መጠቀምና ብክነትን ለመከላከል የሚፈለገውን መጠን ብቻ መጠቀም፣<br>- መሣሪያዎች አገልግሎት ላይ ካልሆኑ ማጥፋት፣ በሚቻል ጊዜ ሁሉ የተፈጥሮ ብርሃንን መመጠቀምና ሌሎች ኀይል ቆጣቢ አሠራሮች፣<br>- ለግንባታ ሠራተኞች ተገቢ የመጸዳጃ/መታጠቢያ ፋሲሊቲዎችን ማቅረብ፣ | የውሃ ጉድጓድ እንዲሁም የጥገና ዕቅድ መኖር | ተቋራጭ፣ ሮሃ | በግንባታ ወቅት | የአ.ማ.ማ.ዕ ላይ የሚገኙትን የመገልገያዎች ተጽዕኖዎች የማስተካከያ እርምጃዎች እንዲተገበር ለኮንትራክተሩ | 600,000 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | - የፍሳሽ ማፋሰሻዎች ከሚደፍን ነገር ነፃ መሆናቸውን ለማረጋገጥ መደበኛ ፍተሻ ማድረግ፣ | | | | ኢ.ማ.ተ.ግ እንዲሰጠው ተደርጓል።<br><br>ተቋራጩና ባለቤቱ መደበኛ ፍተሻዎችን አከናውነዋል። | |
| **የእንቅስቃሴ ፍሰት ተጽዕኖ** | - ለሌሎች ተሽከርካሪዎች ከባድ ፍሰት እንዳለ የሚገልጹ ምልክቶችን በመስከ ዙሪያ ማኖርና የፍጥነት ወሰን ማስቀመጥ፣<br>- ሁሉም አሽከርካሪዎች የፍጥነት ደንቦችን እንደሚያከብሩ ማረጋገጥ፣<br>- ግንባታው መንገዱን እንደማይነካና የትራፊክና የመሬት ወሰን ግዴታዎችን ያከበረ መሆኑን ማረጋገጥ፣<br>- ሁሉም የፕሮጀክት ተሽከርካሪዎች በሕግም ሆነ ከታሰበላቸው ጥቅም አንጻር በጥሩ የቴክኒክ አቋም ላይ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣ | የአደጋዎች ቁጥር | ተቋራጭ፣ ሮሃ | ግንባታ | የአ.ማ.ማ.ዕ ላይ የሚገኙትን የመገልገያዎች ተጽዕኖዎች የማስተካከያ እርምጃዎች እንዲተገበር ለኮንትራክተሩ ኢ.ማ.ተ.ግ እንዲሰጠው ተደርጓል።<br><br>ተቋራጩና ባለቤቱ መደበኛ ፍተሻዎችን አከናውነዋል።<br><br>የትራፊክ ዝውውር ዕቅድ ተዘጋጅቷል፣ በግንባታ ሳይቱ ምልክቶች ዙሪያ ተደርገዋል<br><br>ምንም አደገጋ አልተከሰተም | 500,000 |
| **የሠራተኞች ጤናና ደኅንነት ስጋቶች** | - የሠጤደ ስጋቶችንና የማስተካከያ ስትራቴጂ የሚያካትት ዕቅድ ሥራ ላይ ማዋል፣<br>- ለሁሉም ሠራተኞች በመደበኛነት የጤናና የደኅንነት ሥልጠናዎችን መስጠት፣<br>- የበርካታ ተሽከርካሪዎችን እንቅስቃሴ የሚቀንስ የሥራ የጊዜ ሰሌዳ ማዘጋጀት፣<br>- መደበኛ የመሣሪያ ፍተሻና ጥገና፣<br>- አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉ ነገሮች (ለምሳሌ፡- ተንቀሳቃሽ የማሽን ክፍሎች) ምልክት እንደተደረገባቸው ማረጋገጥ<br>- በመሣሪያ ሊደርስ ስለሚችል አደጋ ለሠራተኞች ግንዛቤ ማስጨበጥና በቂ የአጠቃቀም ሥልጠና መስጠት፣<br>- ለሠራተኞች በቂ የግል ደኅንነት መጠበቂያዎችን (ግደመ) መስጠትና ሲያልቁ ለመተካት በመደበኛነት መከታተል፣<br>- ስጋቶች ባሉባቸው ቦታዎች ሁሉ የሚታዩና የሚነበቡ ምልክቶችነን ማስቀመጥ፣<br>- ወደ ሳይቱና በሳይቱ ዙሪያ የሰዎችን እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር በቂ ጥበቃ ማስቀመጥ፤<br>- በመስክ ላይ ደኅነንቱ የተጠበቀ የመሣሪያዎች ማስቀመጫ/ማከማቻ ማድረግ፣<br>- የሚታዩና የሚነበቡ የተሽከርካሪ እንቅስቃሴ መቆጣጠሪያ ምልክቶችን ማኖርና በሳይቱ ውስጥና ዙሪያ ለአሽከርካሪዎችና እግረኞች ይህንኑ ማሳወቅ፣ | የአደጋዎች ቁጥር፣<br>የግደመ መኖር፣<br>የሥልጠና መሰጠት | ተቋራጭ፣ ሮሃ | ግንባታ | የአ.ማ.ማ.ዕ ላይ የሚገኙትን የሠጤደ ስጋቶችን ለማስቀረትና የማስተካከያ እርምጃዎች እንዲተገበር ለኮንትራክተሩ ኢ.ማ.ተ.ግ እንዲሰጠው ተደርጓል።<br><br>ተቋራጩና ባለቤቱ መደበኛ ፍተሻዎችን አከናውነዋል።<br>የፕሮጀክቱ ባለቤትና ተቋራጩ የሠጤዕ አዘጋጅተዋል።<br><br>የግደመ አሉ።<br><br>ሥልጠናዎች በየጊዜው ይሰጣሉ። | 3,500,000 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | - የእሳት መቆጣጠሪያ መሣሪያዎችን በቀላሉ ማግኘት በሚቻልባቸው ቦታዎች ማስቀመጥና ስለ አጠቃቀማቸው በቂ ሥልጠና ለሠራተኞች መስጠት፣ በመደበኛነት መጠገን፣<br>- ኬሚካሎችንና ማቴሪያሎችን በሚፈጥሩት የስጋት ዓይነት መሠረት ምልክት ማድረግ፣<br>- ደኅንነታቸው የተጠበቀና በቂ የእሳትና የድንገተኛ ሁኔታ የመሰባሰቢያ ቦታዎችን ማዘጋጀትና በተገቢው መንገድ ምልክት የተደረገባቸው መሆኑን ማረጋገጥ፣<br>- የአደጋ ጊዜ አሠራሮችን መዘርጋትና ሠራተኞችን ማሠልጠን፣ መደበኛ ልምምዶችን መሥራት፣ አጎራባች ነዋሪዎችንም ማሳተፍ<br>- የመጀመሪ ርዳታ ኪቶችን ማቅረብ | | | | | |
| **የአየር ብክለት** | - በቤት ውስጥም ሆነ በውጭ የሚኖርን የአየር ብክለት በየሩብ ዓመቱ ማድረግ ያስፈልጋል፤<br>- የማቃጠያ ፊልተሮች በየዓመቱ መፈተሸና እንደ አስፈላጊነቱ መቀየር አለባቸው፣<br>- ፖሊክሎሪኔትድ ዲቤንዞ-ዳዮክሲንስ ያሉባቸው ውጋጆችና ፖሊካርቦኔትድ ዲቤንዞ ፊውራንስ ልየታ ማድረግ ግዴታ ነው፤ እነዚህ ዓይነት ውጋጆች በፍጹም መቃጠል የለባቸውም።<br>- ውጋጆች ወደ ማቃጠያው የሚጨመሩት በመጨረሻው የማቀጣጠያ ክፍል ውስጥ ተፈላጊው የሙቀት መጠን ላይ ከተደረሰ በኋላ ብቻ ነው፤<br>- የውጋጅ መጨመሪያ ሥርዓቱ ከሙቀት መከታተያና መቆጣጠሪያ ሥርዓቱ ጋር እንዲናበብ በማድረግ የሙቀት መጠኑ ከተፈላጊው በታች ከሆነ ተጨማሪ ውጋጅ ወደ ማቃጠያው እንዳይገባ ማድረግ ያስፈልጋል።<br>- የአሲድ ጋዞችን፣ ፓርቲኪዩሌት ማተርንና የሌሎች አየር በካዮችን ልቀት ለመቆጠር የፍሉ ጋዝ ማከሚያ ሥርዓት ይዘረጋል፤<br>- ተገቢ የውጋጅ ቅነሳና ልየታ ሥርዓት ይዘረጋል፤<br>- በምክረ-ሀሳቡ መሠረት ተገቢ የማቃጠያ “ሳይቲንግ”፤<br>- በምክረ-ሀሳቡ መሠረት ተገቢ የማቃጠያ ንድፍ፤ | ሪፖርት፣ በአካል በመገኘት መቃኘት | ሮሃ | በማቃጠያ ኦፐሬሽን ወቅት | | 11,970,000<br><br>ለማቃጠያ ወይም ለማጣሪያ ሥርዓት የሚውል የካፒታል ወጪን ያካትታል |
| **የድምጽ ብክለት** | - ድምጹን ከምንጩ ለማለየየት ቀጣይ ሙሌት (ኢንሱሌሽን) መጠቀም፤<br>- የውጭ ግድግዳዎችና የጣሪያ ንድፎች በአውሮፕላን/ሄሊኮፕተር እንቅስቃሴ የሚፈጠር የድምጽ ብክለት ተጽዕኖን የሚቀንሱ መሆን አለባቸው፣<br>- የግድግዳና የጣሪያ-ኮርኒስ አሴምብሊዎች የደጅ-ቤት ውስጥ ትራንስሚሽን ክላስ ሬቲንግ 40 ወይም ከዚያ በላይ ወይም የድምጽ ትራንስሚሽን ክላስ ሬቲንግ 50 ወይም ከዚያ በላይ ሊኖራቸው፣ የሕንጻው አካል የሆነ መስኮት ደግሞ ከላይ ከተቀመጡት ሬቲንጎች በአንዳቸው 30፤ ወይም ከ10,000 ኮመርሻል ጀት አውሮፕላኖች በላይ ከሚያስተናግዱ አየር ማረፊያዎች በ 5 ማይል (8 ኪሜ) ርቀት ውስጥ ወይም ከፈጣን መንገዶች በ1000 ጫማ (300 ሜትር) ርቀት ውስጥ ያሉ ሕንጻዎች ከሆኑ ደግሞ ከዚያ በላይ ሊኖራቸው ይገባል፤ | ሪፖርት፣ በአካል በመገኘት መቃኘት፣ የቅሬታዎች ብዛት | ሮሃ | ኦፐሬሽን | | 600,000 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | - የድምጽ መጠኖች ከድምጽ ገደብ በሚያልፉበት ጊዜ እንደ ማሞቂያ፣ ጄኔሬተር ያሉ መሣሪያዎችን ለብቻ መለየትና በእነዚህ መሣሪያዎች አካባቢዎች ለሚሠሩ ሠራተኞች የጆሮ መሸፈኛ ማቅረብ፤<br>- የሚፈቀዱ የድምጽ መጠኖች ከፍ ያሉ ከሆኑ ከፍተኛ ድምጽ ያላቸውን ተግባራት ቀን ቀን ማከናወን፤<br>- ዝቅተኛ የድምጽ ሬቲንግ ወይም የድምጽ መቀነሻ ቴክኖሎጂ ያሏቸውን መሣሪያዎች መጠቀም፣<br>- መሣሪያዎችንና ማሽኖችን እንዲሁም ጀነሬተሮችን በማንዋሎቻቸቸው መሠረት በመደበኛነት መጠገን። | | | | | |
| **የውሃ ሀብት ተጽዕኖ** | - ኤፍሉዌንትስ (ሁሉም ሜዲካል ፈሳሽ ውጋጆች) ወደ አካባቢው ከመለቀቃቸው በፊት ማከም፤<br>- በሲንክ ማፋሰሻዎች የሚወጣው ውሃ ወደ ፍሳሽ ሥርዓቱ እንዲገባ ከመደረጉ በፊት ወደ ማጠራቀሚያ ታንከር ገብቶ በጸረ-ተዋህሲያን ይታከማል።<br>- ዝቃጭ ወደ ኮተቤ የማከሚያ ፕላንት በቫኪዩም ካሚዮኖች ይጓጓዛል፤<br>- በማንኛውም ስርገት (ሊኬጅ) ምክንያት ብክለት እንዳይኖር የስርጭት ቦታ የውሃ ጥራት ፍተሻ ይደረጋል።<br>- በጎርፍ ውሃና በጠጣር ውጋጅ መካከል ንክኪ እንዳይኖር ተገቢ የጠጣር ቆሻሻ አያያዝ ሊኖር ይገባል፤<br>- የተቃጠለ አመድ የሚወገደው ደኅንነታቸው በተጠበቁ ቦታዎች በብቻ ነው፤<br>- የጎርፍ ውሃ ማፋሰሻዎች ከኤፍሉወንት ማፋሰሻዎች የተለዩ መሆን አለባቸው፣<br>- በቴክኒካል መመዘኛው መሠረት መደበኛ የማከሚያ ፕላንት ክትትል<br>- የጎርፍ ውሃ ሥርዓቱ በዓመቱ ከከባድ ዝናብ በፊት መፈተሽና መጸዳት አለበት።<br>- ምርጥ ተሞክሮዎችን ሥራ ላይ በማዋል የውሃ ብክነትን መከላከልና ኪሳራን መቀነስ፤<br>- የስርገት (ሊኬጅ) መለያ ሲስተም በመግጠም ከማከሚያ ፕላንቱ የሚመጣ ውሃ እንዳይባክን መከላከል፤ እንዲሁም<br>- የውሃ ማከሙን ሥራ ቅልጥፍናና የታከመውን ውሃ ጥራት ለመፈተሽ በየስድስት ወሩ መደበኛ ክትትል ማድረግ | እንደ አስፈላጊነቱ የላብራቶሪ ፍተሻ፣ ሪፖርት እና በአካል በመገኘት መቃኘት | ሮሃ | ኦፕሬሽን | | 35,000,000 |
| **በአፈር ላይ የሚደርስ ተጽዕኖ** | - ኤፍሉዌንትስ (ሁሉም ሜዲካል ፈሳሽ ውጋጆች) ወደ አካባቢው ከመለቀቃቸው በፊት ማከም፤<br>- በሲንክ ማፋሰሻዎች የሚወጣው ውሃ ወደ ፍሳሽ ሥርዓቱ እንደደዲገባ ከመደረጉ በፊት ወደ ማጠራቀሚያ ታንከር ገብቶ በጸረ-ተዋህሲያን ይታከማል።<br>- በሰነዱ ውስጥ በተቀመጠው ምክረ-ሀሳብ መሠረት ተገቢ የጠጣርና የፈሳሽ ውጋጆች አያያዝ፣<br>- ኬሚካልና ባዮሜዲካል ውጋጆች የኢትዮጵያ መንግስት ባስቀመጣቸው መመሪዎች መሠረት ማስወገድ ያስፈልጋል፤ | ሪፖርት፣ በአካል ተገኝቶ መቃኘት | ሮሃ | ኦፕሬሽን | | 17,000,000 |
| **የመገልገያዎች ተጽዕኖ** | - የውሃ ቁጠባ ቴክኒኮችን በመጠቀምና የሚፈለገውን መጠን ብቻ በመጠቀም የውሃ ብክነትን መከላከል፣ | ሪፖርት | ሮሃ | ኦፕሬሽን ፌዝ | | 8,550,000 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | - የውሃ ጉድጓዶችን ቆፍሮ በአማራጭ የውሃ ምንጭነት መጠቀም፣<br>- ሥራ ላይ ባልሆኑበት ጊዜ መሣሪዎችን በማጥፋት፣ የተፈጥሮ ብርሃንን በመጠቀምና ሌሎች የቁጠባ መንገዶችን በመጠቀም ወዘተ ኀይልን መቆጠብ<br>- ለአነስተኛ ኦፐሬሽኖች የፀሐይ ኀይልን መጠቀም፣<br>- በመደበኛ ኦፐሬሽኖች ወቅት የሚፈለገውን የውሃ መጠን ብቻ መጠቀም፣<br>- የውሃና ኤሌክትሪክ ኀይል ቁጠባ ምልክቶችን ማስቀመጥ፣<br>- ከፍተኛ የኀይል ቅልጥፍና (ኢፊሽንሲ) ያላቸውን ማሽኖችና መሣሪያዎች መጠቀም እንዲሁም ቅልጥፍናቸውን ለማስቀጠል በየጊዜው ጥገና ማድረግ እንዲሁም ለሠራተኞች የውሀና የኀይል ቁጠባ ግንዛቤን መፍጠር፣ | | | | | |
| **የእንቅስቃሴ ፍሰት ተጽዕኖ** | - ወደ መስክ ውስጥና ከመስክ ለመውጣት የሚደረግን የተሽከርካሪዎችን እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር የሚታዩና ግልጽ ምልክቶችን ማስቀመጥ፣<br>- ለድንገተኛ ጊዜ ኦፐሬሽኖችና ለሠራተኞች ከዋናው በር ይልቅ አማራጭ መውጫና መግቢያዎችን ማዘጋጀት፣<br>- በሳይቱ ዙሪያ ያለውን ከፍተኛ የትራፊክ ፍሰት የሚያመለክቱና የፍጥነት ወሰንን የሚያሳዩ ምልክቶችን ማስቀመጥ፣<br>- ሁሉም የፕሮጀክቱ አሽከርካሪዎች የትራፊክ ሕጎችን እንደሚያከብሩ ማረጋገጥ፣<br>- ሁሉም ተሽከርካሪዎች በሕግ በተቀመመጠውና ለታለሙበት ዓላማ በሚሆን ጥሩ የቴክኒክ አቋም ላይ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣ | ሪፖርት፣ በአካል በመገኘት መቃኘት | ሮሃ | ኦፐሬሽን | | 600,000 |
| **የሥራ ቦታ ደኅንነትና የማኅበረሰብ ጤና ተጽዕኖዎች** | - የሠጤደ/ሥደጤ ዕቅዱን በሥራ ላይ ማዋል፣<br>- ለላብራቶሪ ሠራተኞች ስለ መሣያዎች አጠቃቀምና አያያዝ ቴክኒኮች ሥልጠና መስጠት፣<br>- የሮሃ "ሄፓ ፊልተሮች" በየዓመቱ መፈተሸና እንደ አስፈላጊነቱ መቀየር አለባቸው፣<br>- የናሙና እና የውጋጅ አያያዝ፣ ማጓጓዝና ክምችትን የሚመለከት ሥልጠና ይሰጣል፣<br>- ሁሉም ዕቃዎች በአውቶክሌቭ ወይም በኬሚካል ዲስኢንፌክሽን መጸዳት አለባቸው፣<br>- ቀጣይነት ያለው የሥራ ቦታ ጤንነትና ደኅንነት ሥልጠና ለሁሉም ሠራተኞች መስጠት፣<br>- አደጋ ሊፈጥሩ በሚችሉ አካባቢዎች ውስጥ ወይም መሣሪያዎች ላይ ለሚሠሩ ሠራተኞች ግደመ ይቀርባል፣ የግደመ ርጅና ሲኖር ይቀየራሉ፣<br>- እንደ አስፈላጊነቱ የሚነበቡ ምልክቶችንና ትእምርቶችን ማስቀመጥ፣<br>- የእሳት መቀቆጣጠሪ መሣሪያዎችን ማቅረብና ሙሉ ለሙሉ የሚሠሩ መሆናቸውን ለማረጋገጥ መደበኛ ጥገና ማድረግ፣<br>- አስጊ ሥራ ለሚሠሩ ሠራተኞች ውጤታማ ክትባቶችንና የሕክምና አማራጮችን ማቅረብ፣<br>- በባዮ ባንክ ማዕከሉ ለሚሠሩ ሠራተኞች ስለ ፓቶጄኒክና የመግደል ዐቅም ያላቸው ኤጀንቶች አያያዝ ልዩ ሥልጠና መስጠት እንዲሁም ብቁ በሆኑ ሠራተኞች አማካኝነት የኢንፌክሽስ ኤጀንቶችና ተጓዳኞች አያያዝ አሠራሮች ቁጥጥር/ክትትል ማድረግ፣ | ሪፖርት፣ በአካል በመገኘት መቃኘት | ሮሃ | ኦፐሬሽን | | በቢዝነስ ሞዴሉ የኦፐሬሽነን ወጪ ውስጥ የተካተተ በመሆኑ እዚህ ጋር የሚገለጽ ዋና ወጪ የለም |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | - የተሰነጠቁ ወይም በትክክል ያልታሸጉ አምፒውሎች ሲወጡ ሊሰበሩ ወይም ሊፈነዱ ስለሚችሉ ኢንፌክሽስ ማቴሪያሎችን የሚይዙ አምፒውሎች በፍጹም በፈሳሽ ናይትሮጅን ውስጥ መጨመር የለባቸውም፣<br>- የእሳትና የድንገተኛ ሁኔታ የመሰባሰቢያ ቦታዎችን መለየትና ሁሉም በመስክ የሚገኙ ሰዎች እንዲያውቋቸው ማድረግ (ለምሳለሌ፡- በአሳንሰር፣ ደረጃዎች ወዘተ ላይ ካርታዎችን በመለጠፍ)፣<br>- ለአደገኛና ተቀጣጣይ ንጥረ-ነገሮች በቂ ማከማቻ ማዘጋጀትና ገቢ/ወጪ ሰውን መቆጣጠር፣<br>- የጤና ክብካቤ ውጋጆችን እንቅስቃሴ፣ አያያዝና አስተዳደር በመከታተል የሡጤደ ስጋት እንደማይፈጥሩ ማረጋገጥ፣<br>- የኢንፌክሽን መከላከያ ኮሚቴ ማቋቋም፣<br>- ኢንፌክሽንን መከላከልና የታካሚ ደኅንነት ስታንዳርዶችን በሥራ ላይ ማዋል፣<br>- ከኤክስ-ሬይ፣ ኤም አር አይ እና አልትራ ሳውንድ ማሽኖች የሚመነጭ ጨረራን ለመከላከከል ተገቢ መከለያዎችን ወይም ልየታዎችን ማድረግ፣<br>- መደበኛ የኤክስ-ሬይ፣ ኤም አር አይ እና አልትራ ሳውንድ ማሽኖች ፍተሻ፣ | | | | | |
| **የውሃ ሀብት ተጽዕኖዎች** | - አደገኛ ያልሆነ ውጋጅ ወደ ተፈቀዱ የማስወገጃ ፋሲሊቲዎች ይወሰዳል፣<br>- የድንገተኛ ፍሰት/መደፋት የምላሽ ዕቅድ፣<br>- በተገቢው ሁኔታ የተመረጡ የዕጽዋት ዝርያዎችን የያዘ “አረንጓዴ መቀነት”፣<br>- ተጽዕኖዎችን ለመቀነስ የዲኮሚሽኒንግ ዕቅድ ማዘጋጀት፣ | በአካል በመገኘት መቃኘት | ሮሃ ፣ ተቋራጭ | ዲኮሚሽን | | 300,000 ራሱን የቻለ የዲኮሚሽኒንግ ዕቅድ የማዘጋጃ ወጪ |
| **የውጋጅ ማመንጨት ስጋቶች** | - አደገኛ ያልሆነ ውጋጅ ወደ ተፈቀዱ የማስወገጀጃ ፋሲሊቲዎች ይወሰዳል፣<br>- የፕሮጀክት መስክ ድልደላ (ሌቭሊንግ).<br>- የፕሮጀክት መስክ ምልሰት፣<br>- ተጽዕኖ ለመቀነስ የዲኮሚሽኒንግ ፕላን ማዘጋጀት፣ | በአካል በመገኘት መቃኘት | ሮሃ ፣ ተቋራጭ | ዲኮሚሽን | | |
| **የሥራ ቦታ ጤናና ደኅንነት ስጋቶች** | - የሥራ ቦታው ጤናማ መሆን አለበት።<br>- ሠራተኞች የኤች አይ ቪን እና ሌሎች በደም የሚተላለፉ በሽታ አምጪዎችን ሥርጭት የመከላከያ እርምጃዎች መውሰድ አለባቸው፣<br>- ተገቢ የጤና ሥልጠና ለሠራተኞች መሰጠት አለበት፣ተጽዕኖን ለመቀነስ የዲከኮሚሽኒንግ ዕቅድ ማዘጋጀት፣ | በአካል በመገኘት መቃኘት | ሮሃ ፣ ተቋራጭ | ዲኮሚሽን | | |
| | | | | | **ጠቅላላ** | **52,810,000** |

| የተጽዕኖ መግለጫ | የቀረቡ የማቅለያ እርምጃዎች | የክትትል አምላካቾች | ኃላፊነት ያለባቸው አካላት | የሪፖርት ማቅርቢያ ጊዚ | የሚፈልገው በጀት ዲ/ዋይ፣ የክትትል ወጪ |
|---|---|---|---|---|---|
| **1. ቅድመ-ግንባታ እና ግንባታ** | | | | | |
| **የልማት ተነሺዎች** | - ከነዋሪዎቸች ጋር ስለ መልሶ መስፈር ሒደቱ መመካከር ያስፈልጋል።<br>- ለ8 አባወራዎች መ.ማ.ዕ እና መምዕ መዘጋጀትት አለበተት።<br>- ፕሮጀክቱ ለ129 አባወራዎች የመተዳደሪያ ማሻሻያን የሚያካትት የመ.ማ.ዕ እየተገበረ ይገኛል። ፕጀክቱ ለጨረቃ ሰፋሪዎች የመተዳደሪ ድጋፍ፣ የክሂሎት ሥልጠና ይሰጣል። በሜዲካል ካምፐሱ ግንባታና አፕሬሽን ወቅት ሠራተኞችን ከአካባቢው ነዋሪዎች ይቀጥራል።<br>- ለልማት ተነሺዎች በተለይም ለ8 አባወራዎች አፋጣኝ ምትክ ቦታ ሊሰጥ ይገገባለል።<br>- ለልማት ተነሺዎች (በተለይም የከብት እርባታ ላይ ለመሰማራት ፍላጎት ያሳዩት ስለመተዳደሪያ ተግባራት ምክር ሊሰጣቸው ይገባል። | ከማኅበረሰቡ ጋር ምክክር | ከማኅበረሰቡ ጋር ምክክር | በየስድስት ወሩ | 5,000 |
| **የአየር ብክለት** | - አላስፈላጊ የተሽከርካሪ እንቅስቃሴዎችን ማስቀረትና ተገቢ የጊዜ ሰሌዳ ማስቀመጥ<br>- በ “ፒስታ” መንገዶች ላይ የተሽከርካሪዎችን ፍጥነት መገደብ፤<br>- መሣሪያዎችንና ተሽከርካሪዎችን በአግባቡ ጠግኖ በመያዝ ከመጠን ያለፈ ልቀትን ማስቀረት፣<br>- በኦፕሬሽን ወቅት የአቧራ ብክለትን ለመቀነስ የተቆፈሩ ቦታዎች ላይ በየጊዜው ውሃ ማርከፍከፍ<br>- የግንባታ ሥራው መከናወን ያለበት በአግባቡ በተመዘገበ፣ ስለ አካባቢ ጥበቃ ግንዛቤ ባለውና ኀላፊነት በሚሰማው ተቋራጭ መሆን አለበት።<br>- የግል ደኅንነት መጠበቂያዎች (ግደመ) ለሠራተኞች እንዲቀርቡ ማድረግና ሠራተኞችም እንዲጠቀሟቸው ማስገደድ ያስፈልጋል።<br>- አቧራን ለመቀነስ ግብአቶች ከገልባጮች ላይ ሲገለበጡ ከተገቢው ከፍታ መሆን አለበት።<br>- ከባድ መኪኖች ዋና የካርቦን ሞኖክሳይድና የናይትሪክ አክሳይድ ምንጭ በመሆናቸው ብክለቱን ለመቀነስ በተገቢው መንገድ በመደበኛነት መጠገን አለባቸው።<br>- የአቧራ ብናኝ ትንፈሳን ለመቀነስ ለሠራተኞች የፊት ማስክ መቅረብ አለበት።<br>- ለግንባታ መሣሪያዎችና ተሽከርካሪዎች ዝቅተኛ የሰልፈር መጠን ያለውን ናፍጣ መጠቀም<br>- የግንባታ ዕቃዎችንና ፍርስራሽ የጫኑ ተሽከርካሪዎች በሸራ መሸፈን አለባቸው<br>- ጥሬ ዕቃዎች፣ ተቆፍሮ የወጣ ዐፈርና ሌሎች በናኞች መከማቸትም ሆነ መጓጓዝ ያለባቸው በተሸፈኑ መረቦች ሥር መሆን አለበት፤<br>- አቧራ እንዳይነሳ ለማድረግ ከቁፋሮ በፊትና በኦፕሬሽን ወቅት በመደበኛነት ውሃ መርጨት፤<br>- በግንባታ ላይ ያሉ መዋቅሮችን በአቧራ መከላከያ መረቦች መሸፈን<br>- በማንዋሉ መሠረት ማሽኖችንና ሞተሮችን በመደበኛነት መጠገን፤ | የ “በፈር ዞን” (የአካባቢ መከለያ ዞን) ተለይቷል፣ ተከብሯል<br><br>ከማኅበረሰብ የሚመጣ ቅሬታ<br><br>የአቧራ መፈጠር | ሮሃ<br><br>ተቋራጭ | በየስድስት ወሩ | 5,000 |
| **የድምጽ ብክለት** | - በማንዋሉ መሠረት መሣሪያዎችን በትክክለኛው ጊዜ መጠገን፤<br>- ከመደበኛ የሥራ ሰዓት ውጪ የሚከናወን የግንባታ ሥራ የፕሮጀክት አስተዳዳሪውን ፈቃድ ማግኘትና አስፈላጊ ሲሆን በአቅራቢያ ላሉ ነዋሪዎች ማስጠንቀቂያ መስጠት ያስፈልጋል፤<br>- ከ85 ዴሲቤል በላይ የሆኑ ድምጾች የሚፈቀዱት አስቀድመው የጸደቁ ከሆኑና ለአቅራቢው ነዋሪዎች ማስጠንቀቂያ (ቢያንስ ከ2 ቀን በፊት) ከተሰጠ ብቻ ነው፤ | ቅሬታ<br><br>በአካል በመገኘት መቃኘት | ተቋራጭ፣ ሮሃ | በየስድስት ወሩ | 5,000 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | - ከፍተኛ ረብሻ የሚፈጥር ድምጽ ያለው ሥራ መከናወን ያለበት ቀን ብቻ ሲሆን ከላይ የተቀመጠው ማስጠንቀቂያ መሰጠት አለበት፤<br><br>- በግንባታ ሳይቶች ላይ የድምጽ ብክለትን ለመቀነስ የናፍጣ ጀነሬተሮች የድምጽ ማፈኛ ሽፋን ሊኖራቸው ይገባል፤<br>- በቁፋሮ ሳይቶች፣ የፈረሳ ሳይቶች ላይ ጊዜያዊ የድምጽ መከላከያዎችን ማድረግ፤<br>- ከፍተኛ ድምጽ ባለባቸው ቦታዎች ላይ በሚሠሩ ወይም ከፍተኛ ድምጽ ባላቸው መሣሪያዎች አካባቢ ለሚሠሩ የጆሮ መሸፈኛና ሌሎች መጠበቂያ መሣሪያዎችን መስጠት<br>- የግንባታ ሥራዎች በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ብቻ መከናወን አለባቸው፤ | | | | |
| **የውሃ ሀብት ብክለት** | - በውሃ ማጠራሚያ ታንከሮች የሚሰርቅ ፍሳሽ እንዳይኖር በየጊዜው መፈተሽ፣<br>- ተቆፍሮ የወጣ አፈር፣ ጥሬ ዕቃና የግንባታ ብናኝ እንዳይቆለል ተገቢውን የአያያዝና የአወጋገድ መመንገድ መከተል፣<br>- በኮንክሪት ርጭት ወቅት በመርጫ በመርጨት አላስፈላጊ ፍሰትን መቀነስ፣<br>- በጎርፍ ውሃ ማፋሰሻ ውስጥ የሚጠራቀመውን አፈር ለማስቀረት የጎረርፍ ውሃ ማፋሰሻን የአሸዋ ከረጢት ካለባቸው የዝቃጭ ማጠራቀሚያዎች ጋር ማዘጋጀት<br>- ከሠራተኞች ካምፕ የሚመጣ ፍሳሽ ወደ ውሃ አካላት እንዳይገባ ለመከለከል ሴፕቲክ ታንኮችን መገንባት፣<br>- ውጋጆች ከቀሪ (run-off) ውሃ ጋር ተቀላቅለው ወደ ውሃ አካላት እንዳይገቡ ለመከላከል የግንባታና የነዋሪዎች ውጋጅን በተገቢው መንገድ መሰብሰብ፣ ማስተዳደርና ማስወገድ እንዲሁም<br>- የግንባታ ተሸከርካሪዎችና ማሽኖች የዘይት ፍሳሽ እንዳላቸው በየጊዜው መፈተሽ ይኖርባቸዋል። | የላብራቶሪ ፍተሻ፣ እንደ አስፈላጊነቱ የመስክ ቅኝት | ተቋራጭ፣ ሮሃ | በየሦስት ወሩ | 10,000 |
| **የአፈር ተጽዕኖዎች** | - ከምችቶች በኋላ የተክል ዕድገትን በሚገድቡ ማለስለሻ ቅባቶች፣ ናፍጣ፣ ቤንዚን፣ ቆሻሻ ወይም ሌላ መበከል የለባቸውም፤<br>- የማንኛውንም ኬሚካል መደፋትና መፍሰስን ይከላከሉ፤<br>- ሽርሽራን ለመካለከል የአፈር ጥበቃ እርምጃዎችን መውሰድ። በቁፋሮ አካባቢዎች ዙሪያ ጉድጓድ በመቆፈር ዕላፊ ውሃ ወደ ዝቅተኛ አካባቢ እንዳይፈስ ይከላከሉ። ሽርሽራን ለመከላከል በዝናብ ወቅት ቁፋሮ አያከናውኑ፤ የናፍጣና የሃይድሮሊክ ዘይት ፍሳሽ ለመከላከከል ለመሣሪያዎች መደበኛ ጥገና ያድርጉ፤<br>- የነዳጅ ማከማቻው አካባቢ በአግባቡ መነጠፍ/መጠረግ አለበት፤<br>- የግንባታ ብናኞች በተሸፈኑ ማከማቻዎችና በተነጠፉ ቦታዎች ሥር መቀመጥ አለባቸው። ለዚሁ በተለዩ ሳይቶች ላይ መወገድ አለባቸው።<br>- ከሠራተኞች ካምፕ የሚመጣ ፍሳሽ መስክ ላይ ሊለይ ይችላል። የምግብ ውጋጅ/ርጥብ ውጋጅ በሳይቱ ላይ በሚገኙ ጉድጓዶች ውስጥ ኮምፖስት መደረግ አለበት።<br>- ሪሳይክል የሚደረግ ውጋጅ ፈቃድ ላላቸው ነጋዴዎች መሸጥ፤ ቀሪው ደግሞ የውጋጅ አስተዳደር ኀላፊነት ባላቸው የአካባቢው የመንግስት አካላት አማካኝነተት እንዲወገድ መደረግ አለበት።<br>- ተገቢ የጠጣር ውጋጅ አያያዝ አሠራር (ልየታ፣ መሰብሰብ፣ ማጓጓዝ፣ መልሰሶ መጠቀም፣ ሪሳይክከል፣ መልሶ ማግኘትና ማስወገድ) መኖር አለበት። | የመስክ ቅኝት፣ የላይኛው ንጣፍ አፈር ክምር መኖር | ተቋራጭ፣ ሮሃ | በየስድስት ወሩ | 4,000 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| **የብዝኀ-ሕይወት ተጽዕኖዎች** | - ፕሮጀክቱ በሳይቱ ውስጥ ከፍተኛ የብዝኀ-ሕይወት ዕሴት ያላቸው እና/ወይም የሥነ--ምኅዳር አገልግሎት የሚሰጡ ልዩ ልዩ አገር በቀል የዛፍ ዝርያዎችን ለመትከል የሚሆን ቦታ በመለየት እንዲሁም የምኅዳር መበታተንን የሚቀንሱ እንደ ባዮሎጂካል ኮሪደር፣ በኦፕሬሽን ወቅት/በኋላ ምኅዳሮችን ወደ ነበሩበት የመመለስ ያሉ ርመምጃዎችን በመውሰድ ይህንን ተጽዕኖ ማቃለል ይችላል።<br>- ብዝኀ-ሕይወትን መጠበቅ፣ የሥነ-ምኅዳር አገልግሎቶችን ማስጠበቅና ሕይወት ያላቸውን የተፈጥሮ ሀብቶች ዘላቂነትን ባማከለ መንገድ ማስተዳደር ለዘላቂ ዕድገት ቁልፍ ናቸው።<br>- የዕጽዋት ምንጣሮ ለመንገድ ጥርጊያና የጉድጓድ ቁፋሮ ተግባራት እስኪሚያስፈልገው ዝቅተኛ መጠን ብቻ መገደብ አለባቸው። የላይኛው አፈር ንጣፍና የዛፎች ጥልቅ ሥርን ማወክ በተቻለ መጠን ዝቅተኛ መሆን አለበት።<br>- ከኦፕሬሽን ሥራዎችን ቀጥሎ የሚከናወኑ የመልሶ ማልማት ተግባራት ተገቢ ቁጥር ያላቸው አገር በቀል ዝርያዎች መተከላቸውንና በመልሶ ማልማት ዕቅዱ መሠረት መከናወናቸውን ማረጋገጥ፤<br>- የገጸ-ምድር የአትክልት ሥፍራዎች፣ ርከኖችንና የዕጽዋትና የአትክልት ሥፍራዎችን ጥበቃ ማከናወን፤<br>- ምንጣሮን በግንባታ ቦታዎች ብቻ መወሰንና ምንጣሮ የማይደረግባቸውን ቦታዎች በምልክት መለየት | የምልሰት ስትራቴጂዎች መኖር | ተቋራጭ፣ ሮሃ | በየስድስት ወሩ | 3,000 |
| **የመገልገያ ተጽዕኖዎች** | - የውሃ ቁጠባ ቴክኒኮችን መጠቀምና ብክነትን ለመከላከል የሚፈለገውን መጠን ብቻ መጠቀም፣<br>- መሣሪያዎች አገልግሎት ላይ ካልሆኑ ማጥፋት፣ በሚቻል ጊዜ ሁሉ የተፈጥሮ ብርሃንን መመጠቀምና ሌሎች ኀይል ቆጣቢ አሠራሮች፣<br>- ለግንባታ ሠራተኞች ተገቢ የመጸዳጃ/መታጠቢያ ፋሲሊቲዎችን ማቅረብ፤<br>- የፍሳሽ ማፋሰሻዎች ከሚደፍን ነገር ነፃ መሆናቸውን ለማረጋገጥ መደበኛ ፍተሻ ማድረግ፤ | የጉድጓድ መኖር፣ የጥገና ዕቅድ መኖር | ተቋራጭ፣ ሮሃ | በየስድስት ወሩ | 2,000 |
| **የእንቅስቃሴ ፍሰት ተጽዕኖዎች** | - ለሌሎች ተሽከርካሪዎች ከባድ ፍሰት እንዳለ የሚገልጹ ምልክቶችን በመስክ ዙሪያ ማኖርና የፍጥነት ወሰን ማስቀመጥ፣<br>- ሁሉም አሽከርካሪዎች የፍጥነት ደንቦችን እንደሚያከብሩ ማረጋገጥ፣<br>- ግንባታው መንገዱን እንደማይነካና የትራፊክና የመሬት ወሰን ግዴታዎችን ያከበረ መሆኑን ማረጋገጥ፣<br>- ሁሉም የፕሮጀክት ተሽከርካሪዎች በሕግም ሆነ ከታሰበላቸው ጥቅም አንጻር በጥሩ የቴክኒክ አቋም ላይ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤ | የአደጋዎች ቁጥር | ተቋራጭ፣ ሮሃ | በየሦስት ወሩ | 6,000 |
| **የጤና የደኅንነትና አካባቢ ስጋቶች** | - የሠጤደ ስጋቶችንና የማስተካከያ ስትራቴጂ የሚያካትት ዕቅድ ሥራ ላይ ማዋል፣<br>- ለሁሉም ሠራተኞች በመደበኛነት የጤናና የደኅንነት ሥልጠናዎችን መስጠት፣<br>- የበርካታ ተሽከርካሪዎችን እንቅስቃሴ የሚቀንስ የሥራ የጊዜ ሰሌዳ ማዘጋጀት፣<br>- መደበኛ የመሣሪያ ፍተሻና ጥገና፤<br>- አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉ ነገሮች (ለምሳሌ፡- ተንቀሳቃሽ የማሽን ክፍሎች) ምልክት እንደተደረገባቸው ማረጋገጥ<br>- በመሣሪያ ሊደርስ ስለሚችል አደጋ ለሠራተኞች ግንዛቤ ማስጨበጥና በቂ የአጠቃቀም ሥልጠና መስጠት፣<br>- ለሠራተኞች በቂ የግል ደኅንነት መጠበቂያዎችን (ግደመ) መስጠትና ሲያልቁ ለመተካት በመደበኛነት መከታተል፤<br>- ስጋቶች ባሉባቸው ቦታዎች ሁሉ የሚታዩና የሚነበቡ ምልክቶችነን ማስቀመጥ፣<br>- ወደ ሳይቱና በሳይቱ ዙሪያ የሰዎችን እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር በቂ ጥበቃ ማስቀመጥ፤ | የአደጋዎች ቁጥር፣ የግደመ መኖር፣ የሥልጠና መሰጠት | ተቋራጭ፣ ሮሃ | በየሦስት ወሩ | 10,000 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | - በመስክ ላይ ደኅንነቱ የተጠበቀ የመሣሪያዎች ማስቀመጫ/ማከማቻ ማድረግ፣<br>- የሚታዩና የሚነበቡ የተሽከርካሪ እንቅስቃሴ መቆጣጠሪያ ምልክቶችን ማኖርና በሳይቱ ውስጥና ዙሪያ ለአሽከርካሪዎችና እግረኞች ይህንኑ ማሳወቅ፣<br>- የእሳት መቆጣጠሪያ መሣሪያዎችን በቀላሉ ማግኘት በሚቻልባቸው ቦታዎች ማስቀመጥና ስለ አጠቃቀማቸው በቂ ሥልጠና ለሠራተኞች መስጠት፣ በመደበኛነት መጠገን፣<br>- ኬሚካሎችንና ማቴሪያሎችን በሚፈጥሩት የስጋት ዓይነት መሠረት ምልክት ማድረግ፣<br>- ደኅንነታቸው የተጠበቀና በቂ የእሳትና የድንገተኛ ሁኔታ የመሰባሰቢያ ቦታዎችን ማዘጋጀትና በተገቢው መንገድ ምልክት የተደረገባቸው መሆኑን ማረጋገጥ፣<br>- የአደጋ ጊዜ አሠራሮችን መዘርጋትና ሠራተኞችን ማሠልጠን፣ መደበኛ ልምምዶችን መሥራት፣ አጎራባች ነዋሪዎችንም ማሳተፍ<br>- የመጀመሪ ርዳታ ኪቶችን ማቅረብ | | | | |
| **2. የኦፕሬሽን ፌዝ ተጽዕኖዎች** | | | | | |
| **የአየር ብክለት** | - በቤት ውስጥም ሆነ በውጭ የሚኖርን የአየር ብክለት በየሩብ ዓመቱ ማድረግ ያስፈልጋል፤<br>- የማቃጠያ ፊልተሮች በየዓመቱ መፈተሽና እንደ አስፈላጊነቱ መቀየር አለባቸው፣<br>- ፖሊክሎሪኔትድ ዲቤንዞ-ዳዮክሲንስ ያሉባቸው ውጋጆችና ፖሊካርቦኔትድ ዲቤንዞ ፊውራንስ ልየታ ማድረግ ግዴታ ነው፤ እነዚህ ዓይነት ውጋጆች በፍጹም መቃጠል የለባቸውም።<br>- ውጋጆች ወደ ማቃጠያው የሚጨመሩት በመጨረሻው የማቀጣጠያ ክፍል ውስጥ ተፈላጊው የሙቀት መጠን ላይ ከተደረሰ በኋላ ብቻ ነው፤<br>- የውጋጅ መጨመሪያ ሥርዓቱ ከሙቀት መከታተያና መቆጣጠሪያ ሥርዓቱ ጋር እንዲናበብ በማድረግ የሙቀት መጠኑ ከተፈላጊው በታች ከሆነ ተጨማሪ ውጋጅ ወደ ማቃጠያው እንዳይገባ ማድረግ ያስፈልጋል።<br>- የአሲድ ጋዞችነን፣ ፓርቲኪዩሌት ማተርንና የሌሎች አየር በካዮችን ልቀት ለመቆጠር የፍሉ ጋዝ ማከሚያ ሥርዓት ይዘረጋል፤<br>- ተገቢ የውጋጅ ቅነሳና ልየታ ሥርዓት ይዘረጋል፤<br>- በምክረ-ሀሳቡ መሠረት ተገቢ የማቃጠያ "ሳይቲንግ"፤<br>- በምክረ-ሀሳቡ መሠረት ተገቢ የማቃጠያ ንድፍ፤ | ሪፖርት፣ በአካል በመገኘት መቃኘት | ሮሃ | በየስድስት ወሩ | 8,000 |
| **የድምጽ ብክለት** | - ድምጹን ከምንጬ ለማለያየት ቀጣይ ሙሌት (ኢንሱሌሽን) መጠቀም፤<br>- የውጭ ግድግዳዎችና የጣሪያ ንድፎች በአውሮፕላን/ሄሊኮፕተር እንቅስቃሴ የሚፈጠር የድምጽ ብክለት ተጽዕኖን የሚቀንሱ መሆን አለባቸው፣<br>- የግድግዳና የጣሪያ-ኮርኒስ አሴምብሊዎች የደጅ-ቤት ውስጥ ትራንስሚሽን ክላስ ሬቲንግ 40 ወይም ከዚያ በላይ ወይም የድምጽ ትራንስሚሽን ክላስ ሬቲንግ 50 ወይም ከዚያ በላይ ሊኖራቸው፣ የሕንጻው አካል የሆነ መስኮት ደግሞ ከላይ ከተቀመጡት ሬቲንጎች በአንዳቸው 30፤ ወይም ከ10,000 ኮመርሻል ጀት አውሮፕላኖች በላይ ከሚያስተናግዱ አየር ማረፊያዎች በ 5 ማይል (8 ኪሜ) ርቀት ውስጥ ወይም ከፈጣን መንገዶች በ1000 ጫማ (300 ሜትር) ርቀት ውስጥ ያሉ ሕንጻዎች ከሆኑ ደግሞ ከዚያ በላይ ሊኖራቸው ይገባል፤<br>- የድምጽ መጠኖች ከድምጽ ገደብ በሚያልፉበት ጊዜ እንደ ማሞቂያ፣ ጄኔሬተር ያሉ መሣሪያዎችን ለብቻ መለየትና በእነዚህ መሣሪያዎች አካባቢዎች ለሚሠሩ ሠራተኞች የጆሮ መሸፈኛ ማቅረብ፤ | ሪፖርት፣ በአካል በመገኘት መቃኘት፣ የቅሬታዎች ቁጥር | ሮሃ | በየስድስት ወሩ | 5,000 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | - የሚፈቀዱ የድምጽ መጠኖች ከፍ ያሉ ከሆኑ ከፍተኛ ድምጽ ያላቸውን ተግባራት ቀን ቀን ማከናወን<br>- ዝቅተኛ የድምጽ ሬቲንግ ወይም የድምጽ መቀነሻ ቴክኖሎጂ ያሏቸውን መሣሪያዎች መጠቀም፣<br>- መሣሪያዎችንና ማሽኖችን እንዲሁም ጀነሬተሮችን በማንዋሎቻቸቸው መሠረት በመደበኛነት መጠገን። | | | | |
| **የውሃ ሀብት ተጽዕኖ** | - ኤፍሉዌንትስ (ሁሉም ሜዲካል ፈሳሽ ውጋጆች) ወደ አካባቢው ከመለቀቃቸው በፊት ማከም፤<br>- በሲንክ ማፋሰሻዎች የሚወጣው ውሃ ወደ ፍሳሽ ሥርዓቱ እንዲገባ ከመደረጉ በፊት ወደ ማጠራቀሚያ ታንከር ገብቶ በጸረ-ተዋህሲያን ይታከማል።<br>- ዝቃጭ ወደ ኮተቤ የማከሚያ ፕላንት በቫኪዩም ካሚዮኖች ይጓጓዛል፤<br>- በማንኛውም በመንጠባጠብ(ሊኬጅ) ምክንያት ብክለት እንዳይኖር የስርጭት ቦታ የውሃ ጥራት ፍተሻ ይደረጋል።<br>- በጎርፍ ውሃና በጠጣር ውጋጅ መካከል ንክኪ እንዳይኖር ተገቢ የጠጣር ቆሻሻ አያያዝ ሊኖር ይገባል፤<br>- የተቃጠለ አመድ የሚወገደው ደኅንነታቸው በተጠበቁ ቦታዎች በብቻ ነው፤<br>- የጎርፍ ውሃ ማፋሰሻዎች ከኤፍሉወንት ማፋሰሻዎች የተለዩ መሆን አለባቸው፣<br>- በቴክኒካል መመዘኛው መሠረት መደበኛ የማከሚያ ፕላንት ክትትል<br>- የጎርፍ ውሃ ሥርዓቱ በዓመቱ ከከባድ ዝናብ በፊት መፈተሸና መጸዳት አለበት።<br>- ምርጥ ተሞክሮዎችን ሥራ ላይ በማዋል የውሃ ብክነትን መከላከልና ኪሳራን መቀነስ፤<br>- የስርገት (ሊኬጅ) መለያ ሲስተም በመግጠም ከማከሚያ ፕላንቱ የሚመጣ ውሃ እንዳይባክን መከላከል፤ እንዲሁም<br>- የውሃ ማከሙን ሥራ ቅልጥፍናና የታከመውን ውሃ ጥራት ለመፈተሸ በየስድስት ወሩ መደበኛ ክትትል ማድረግ | አስፈላጊ ከሆነ የላብራቶሪ ፍተሻ፣ ሪፖርትና በአካል ተገኝቶ መቃኘት | ሮሃ | በየሦስት ወሩ | 80,000 |
| **የአፈር ተጽዕኖዎች** | - ኤፍሉዌንትስ (ሁሉም ሜዲካል ፈሳሽ ውጋጆች) ወደ አካባቢው ከመለቀቃቸው በፊት ማከም፤<br>- በሲንክ ማፋሰሻዎች የሚወጣው ውሃ ወደ ፍሳሽ ሥርዓቱ እንደደዲገባ ከመደረጉ በፊት ወደ ማጠራቀሚያ ታንከር ገብቶ በጸረ-ተዋህሲያን ይታከማል።<br>- በሰነዱ ውስጥ በተቀመጠው ምክረ-ሀሳብ መሠረት ተገቢ የጠጣርና የፈሳሽ ውጋጆች አያያዝ፣<br>- ኬሚካልና ባዮሜዲካል ውጋጆች የኢትዮጵያ መንግስት ባስቀመጣቸው መመሪዎች መሠረት ማስወገድ ያስፈልጋል፤ | ሪፖርት፣ በአካል ተገኝቶ መቃኘት | ሮሃ | በየስድስት ወሩ | 6,000 |
| **የመገልገያ ተጽዕኖዎች** | - የውሃ ቁጠባ ቴክኒኮችን በመጠቀምና የሚፈለገውን መጠን ብቻ በመጠቀም የውሃ ብክነትን መከላከል፣<br>- የውሃ ጉድጓዶችን ቆፍሮ በአማራጭ የውሃ ምንጭነት መጠቀም፣<br>- ሥራ ላይ ባልሆኑበት ጊዜ መሣሪዎችን በማጥፋት፣ የተፈጥሮ ብርሃንን በመጠቀምና ሌሎች የቁጠባ መንገዶችን በመጠቀም ወዘተ ኀይልን መቆጠብ<br>- ለአነስተኛ ኦፕሬሽኖች የፀሐይ ኀይልን መጠቀም፣<br>- በመደበኛ ኦፕሬሽኖች ወቅት የሚፈለገውን የውሃ መጠን ብቻ መጠቀም፣<br>- የውሃና ኤሌክትሪክ ኀይል ቁጠባ ምልክቶችን ማስቀመጥ፣<br>- ከፍተኛ የኀይል ቅልጥፍና (ኢፊሽንሲ) ያሏቸውን ማሽኖችና መሣሪያዎች መጠቀም እንዲሁም ቅልጥፍናቸውን ለማስቀጠል በየጊዜው ጥገና ማድረግ እንዲሁም<br>- ለሠራተኞች የውሀሃና የኀይል ቁጠባ ግንዛቤን መፍጠር፣ | ሪፖርት | ሮሃ | በየስድስት ወሩ | 15,000 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| **የእንቅስቃሴ ፍሰት ተጽዕኖዎች** | - ወደ መስክ ውስጥና ከመስክ ለመውጣት የሚደረግን የተሽከርካሪዎችን እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር የሚታዩና ግልጽ ምልክቶችን ማስቀመጥ፣<br>- ለድንገተኛ ጊዜ ኦፐሬሽኖችና ለሠራተኞች ከዋናው በር ይልቅ አማራጭ መውጫና መግቢያዎችን ማዘጋጀት፣<br>- በሳይቱ ዙሪያ ያለውን ከፍተኛ የትራፊክ ፍሰት የሚያመለክቱና የፍጥነት ወሰንን የሚያሳዩ ምልክቶችን ማስቀመጥ፣<br>- ሁሉም የፕሮጀክቱ አሽከርካሪዎች የትራፊክ ሕጎችን እንደሚያከብሩ ማረጋገጥ፣<br>- ሁሉም ተሽከርካሪዎች በሕግ በተቀመመጠውና ለታለሙበት ዓላማ በሚሆን ጥሩ የቴክኒክ አቋም ላይ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣ | ሪፖርት፣ በአካል ተገኝቶ መቃኘት | ሮሃ | በየሦስት ወሩ | 6,000 |
| **የአካባቢ፣ የጤናና ደኅንነት እንዲሁም የማኅበረሰብ ጤና ተጽዕኖዎች** | - የሠጤደ/ሥደጤ ዕቅዱን በሥራ ላይ ማዋል፣<br>- ለላብራቶሪ ሠራተኞች ስለ መሣያዎች አጠቃቀምና አያያዝ ቴክኒኮች ሥልጠና መስጠት፣<br>- የሮሃ "ሄፓ ፊልተሮች" በየዓመቱ መፈተሸና እንደ አስፈላጊነቱ መቀየር አለባቸው፣<br>- የናሙና እና የውጋጅ አያያዝ፣ ማጓጓዝና ክምችትን የሚመለከት ሥልጠና ይሰጣል<br>- ሁሉም ዕቃዎች በአውቶክሌቭ ወይም በኬሚካል ዲስኢንፌክሽን መጸዳት አለባቸው<br>- ቀጣይነት ያለው የሥራ ቦታ ጤንነትና ደኅንነት ሥልጠና ለሁሉም ሠራተኞች መስጠት፣<br>- አደጋ ሊፈጥሩ በሚችሉ አካባቢዎች ውስጥ ወይም መሣሪያዎች ላይ ለሚሠሩ ሠራተኞች ግደመ ይቀርባል፣ የግደመ ርጅና ሲኖር ይቀየራሉ፣<br>- እንደ አስፈላጊነቱ የሚነበቡ ምልክቶችንና ትእምርቶችን ማስቀመጥ፣<br>- የእሳት መቀቆጣጠሪ መሣሪያዎችን ማቅረብና ሙሉ ለሙሉ የሚሠሩ መሆናቸውን ለማረጋገጥ መደበኛ ጥገና ማድረግ፣<br>- አስጊ ሥራ ለሚሠሩ ሠራተኞች ውጤታማ ክትባቶችንና የሕክምና አማራጮችን ማቅረብ፣<br>- በባዮ ባንክ ማዕከሉ ለሚሠሩ ሠራተኞች ስለ ፓቶጂኒክና የመግደል ዐቅም ያላቸው ኤጀንቶች አያያዝ ልዩ ሥልጠና መስጠት እንዲሁም ብቁ በሆኑ ሠራተኞች አማካኝነት የኢንፌክሽስ ኤጀንቶችና ተጓዳኞች አያያዝ አሠራሮች ቁጥጥር/ክትትል ማድረግ፣<br>- የተሰነጠቁ ወይም በትክክል ያልታሸጉ አምፒውሎች ሲወጡ ሊሰበሩ ወይም ሊፈነዱ ስለሚችሉ ኢንፌክሽስ ማቴሪያሎችን የሚይዙ አምፒውሎች በፍጹም በፈሳሽ ናይትሮጅን ውስጥ መጨመር የለባቸውም፣<br>- የእሳትና የድንገተኛ ሁኔታ የመሰባሰቢያ ቦታዎችን መለየትና ሁሉም በመስክ የሚገኙ ሰዎች እንዲያውቋቸው ማድረግ (ለምሳሌ፡- በአሳንሰር፣ ደረጃዎች ወዘተ ላይ ካርታዎችን በመለጠፍ)፣<br>- ለአደገኛና ተቀጣጣይ ንጥረ-ነገሮች በቂ ማከማቻ ማዘጋጀትና ገቢ/ወጪ ሰውን መቆጣጠር፣<br>- የጤና ክብካቤ ውጋጆችን እንቅስቃሴ፣ አያያዝና አስተዳደር በመከታተል የሠጤደ ስጋት እንደማይፈጥሩ ማረጋገጥ፣<br>- የኢንፌክሽን መከላከያ ኮሚቴ ማቋቋም፣<br>- ኢንፌክሽንን መከላከልና የታካሚ ደኅንነት ስታንዳርዶችን በሥራ ላይ ማዋል፣<br>- ከኤክስ-ሬይ፣ ኤም አር አይ እና አልትራ ሳውንድ ማሽኖች የሚመነጭ ጨረራን ለመከላከል ተገቢ መከለያዎችን ወይም ልየታዎችን ማድረግ፣<br>- መደበኛ የኤክስ-ሬይ፣ ኤም አር አይ እና አልትራ ሳውንድ ማሽኖች ፍተሻ፣ | ሪፖርት፣ በአካል ተገኝቶ መቃኘት | ሮሃ | በየሦስት ወሩ | 10,000 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 3. **ዲኮሚሽን ፌዝ ተጽዕኖዎች** | | | | | |
| **የውሃ ሀብት ተጽዕኖዎች** | - አደገኛ ያልሆነ ውኃጅ ወደ ተፈቀዱ የማስወገጃ ፋሲሊቲዎች ይወሰዳል፣<br>- የድንገተኛ ፍሰት/መደፋት የምላሽ ዕቅድ፣<br>- በተገቢው ሁኔታ የተመረጡ የዕጽዋት ዝርያዎችን የያዘ "አረንጓዴ መቀነት"፣ | በአካል ተገኝቶ መቃኘት | ሮሃ ፣ ተቋራጭ | በየሦስት ወሩ | 3,000 |
| **የውኃጅ ማመንጨት ተጽዕኖዎች** | - አደገኛ ያልሆነ ውኃጅ ወደ ተፈቀዱ የማስወገጃ ፋሲሊቲዎች ይወሰዳል፣<br>- የፕሮጀክት መስክ ድልደላ (ሌቭሊንግ).<br>- የፕሮጀክት መስክ ምልሰት፣ | በአካል ተገኝቶ መቃኘት | ሮሃ ፣ ተቋራጭ | በየሦስት ወሩ | 5,000 |
| **የሥራ ቦታ የጤናና የደኅንነት ስጋቶች** | - የሥራ ቦታው ጤናማ መሆን አለበት።<br>- ሠራተኞች የኤች አይ ቪን እና ሌሎች በደም የሚተላለፉ በሽታ አምጪዎችን ሥርጭት የመከላከያ እርምጃዎች መውሰድ አለባቸው፣<br>- ተገቢ የጤና ሥልጠና ለሠራተኞች መስጠት አለበት፣ | በአካል ተገኝቶ መቃኘት | ሮሃ ፣ ተቋራጭ | በየሦስት ወሩ | 6,000 |
| | **ጠቅላላ የክትትል ወጪ** | | | | **194,000** |

## የቅሬታ አፈታት

አብይ ሊባሉ የሚችሉ ቅሬታዎች ይነሳሉ ተብሎ አይጠበቅም። ሆኖም ባለ ድርሻዎች ከየትኛውም የፕሮጀክቱ ገጽታ የሚነሱ ቅሬታዎቻቸው የሚፈቱበትን መንገድ ለማመቻቸት የሚከተሉት የቅሬታ አፈታት መንገዶች ተዘጋጅተዋል። ማኅበረሰቡ ስለ ቅሬታ አፈታት ሥነ-ሥርዓቶች በራሳቸው ቋንቋ እንዲያውቁ ይደረጋል። የቅሬታ አፈታት መንገዶች የሚመለከቱ መረጃዎች ሁሉ ሰዎች ሊመለከቷቸው በሚችሉ ቦታዎችና በሚሰየሙ የማኅበረሰብ ተጠሪዎች ጋር እንዲለጠፉ/እንዲቀመጡ ይደረጋል።

አልሚው/ተቋራጩ በመልሶ ማስፈር ዕቅዱ ትግበራ ወቅት ለቅሬታ አፈታት ብቻ የተለየ ቢሮ እና ቅሬታዎችን ለመስማት የተዘጋጀ የስልክ መስመር ይኖረዋል። አልሚው/ተቋራጩ ከማንኛውም ባለ ድርሻ በአካል፣ በኢሜይል፣ በፖስታ፣ በስል ወይም በማንኛውም አግባብነት ባለው የተግባቦት መስመር በኩል የሚቀርቡ ከፕሮጀክቱ ጋር የሚያያዙ አስተያየቶችን ወይም አቤቱታዎችን በሙሉ ይቀበላል። ደንበኛው/ተቋራጩ አንድ የቅሬታ መኮንን መድቦ የቅሬታዎቹን ዝርዝር እንዲሰማ፣ ቅሬታዎቹን/አስተያየቶቹን የቅሬታ አቅራቢውን ስም፣ ቅሬታው የቀረበበትን ቀን፣ የጉዳዩን አጭር መግለጫ፣ የቀረቡትን የማስተካከያ እርምጃዎችና ለቅሬታ አቅራቢ መልስ የተሰጠበትን ቀን የሚያካትት መዝገብ ላይ በአጭሩ እንዲያሰፍር ያደርጋል።

አልሚው/ተቋራጩ ሁሉንም ቅሬታዎች በ6 የሥራ ቀናት ውስጥ መዝግቦ እንደደረሱት ማረጋገጫ መስጠት እንዲሁም በ15 የሥራ ቀናት ውስጥ ምላሽ መስጠት አለበት። ሁሉም ምላሾች ቅሬታ አቅራቢዎቹ በሚመርጡት የተግባቦት መንገድ መሠረት በጽሑፍ ወይም በንግግር ሊሰጡ ይችላሉ።

## ሚናዎችና ኀላፊነቶች

**የፕሮጀክቱ አልሚ፡-** አካባቢያዊና ማኅበራዊ ተጽዕኖዎችን ማስተዳደርና መከታተል።

**የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን፡--** የአካባቢና ማኅበራዊ ተጽዕኖ ግምገማ የጥናት ሪፖርቱን መገምገምና ማጽደቅ እንዲሁም የአካባቢያዊና ማኅበራዊ ማስተዳደርያ ዕቅዱን አፈጻጸም የመከታተል ኀላፊነት አለበት።

የአካባቢያዊና ማኅበራዊ ማስተዳደሪያ ዕቅዱን እንዲሁም የአካባቢያዊና ማኅበራዊ ማስተዳደሪያና መከታተያ ዕቅድን ጨምሮ ለሁሉም የአካባቢያዊና ማኅበራዊ እርምጃዎች የሚያስፈልገው ጠቅላላ በጀት ግምት ብር 53,004,000.00 ወይም ዩ.ኤስ.ዲ 925,026.178 (1 ዩ.ኤስ.ዲ = 57.3 ብር ምንዛሬ ተመን) ነው።

## አካባቢያዊና ማኅበራዊ አፈጻጸም

በመስክ ቅኝት እንዲሁም በአ.ማ.ማ.ዕ ግምገማ መሠረት ኩባንያው በአካባቢያዊና ማኅበራዊ ተጽዕኖዎች ማስተዳደሪያ ዕቅዱ መሠረት እየተንቀሳቀሰ ነው። የግንባታ እንቅስቃሴዎች ከአየር ብክለት፣ በመደፋት/መፍሰስ ምላሽ ዕቅድ፣ ከመልሶ ማስፈር የድርጊት ዕቅድ፣ ከድንገተኛ ሁኔታ ምላሽ ዕቅድ ዝግጅት፣ ከድምጽ ብክለት፣ ከእንቅስቃሴ ፍሰት ተጽዕኖ እና የሥራ ቦታ አደጋዎች አንጻር ተገምግመዋል። የአፈር ተጽዕኖና የውሃ ሀብት ተጽዕኖ ግምገማው እንቅስቃሴው በከፊል የተሟላ ቢሆንም በአካባቢና ማኅበራዊ ተጽዕኖ ግምገማው ውስጥ በተቀመጡት የማሻሻያ እርምጃዎች መሠረት የማስተካከያ እርምጃዎች መወሰድ አለባቸው።